# የአገራችን የትምህርት ዕድገት

## መግቢያ

በሕገ መንግስታችን ሆነ በትምህርት ፖሊሲያችን የትምህርት አገልግሎት ማግኘት የማንኛውም ዜጋ መብት እንደሆነ ተሰምሮበታል። ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ለማዳረስ የገባቻቸውን የሚሊኒየም የልማት ግቦች (MDG) እና የትምህርት ለሁሉም (EFA) ስምምነቶችን ለማሳካት መላ ህብረተሰቡን በከፍተኛ ደረጃ ያሳተፈ እንቅስቃሴ በመደረጉ በአብዛኛዎቹ ክልሎቻችን የትምህርት ተሳትፎን፣ ፍትሃዊነት፣ አቅርቦትና ስርጭቱን ማረጋገጥና ማሳደግ ተችሏል።

## የቀድሞ ዘመናት የትምህርት ሥርዓት ችግሮች

የኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ረዥም ዕድሜ እንዳለው የሚነገርለት ይሁን እንጂ ሕዝባችን ከትምህርት ውጤት በሚገባ ተጠቃሚ ነበር ለማለት አያስደፍርም፡፡

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ የተወሰኑ ት/ቤቶች የቀለም ትምህርት መስጠት ሲጀመር የነበረው የትምህርት ዓላማ በመንግስት ሥራ የሚሰማሩትንና ተርጓሚዎችን በማፍራት ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር፡፡ በወቅቱ ይሰጥ የነበረው ትምህርት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ለውጥ ሊያስገኝ የሚችል የተማረ የሰው ሀይል የማፍራት ተልዕኮ አልነበረውም፡፡

የጣሊያን ሠራዊት ድል ከተደረገ በኋላ በአዲስ መልክ የተጀመረው ትምህርትም ቢሆን ዋና ዓላማው በአዲስ በተከፈቱ የመንግስት መ/ቤቶች የሚሰራ የቢሮ ሠራተኛ ከማፍራት ውጭ የሀገሪቱን ሕዝቦች ፍላጎት የሚያሟላ ትምህርት ለመስጠት ያለመ አልነበረም፡፡

ከ1935 እስከ 1950 ዎቹ መጀመሪያ ድረስ የነበረው ትምህርት በእንግሊዝ ሥርዓት የተቀረፀ፣ ኢትዮጵያዊ ይዘት ያልነበረው ከመሆኑ ሌላ የገጠሩን ሁኔታ ያገናዘበ፣ የትምህርት አቅርቦትን ለማስፋት፣ የሕብረተሰቡን ኑሮ ሁኔታ ለመለወጥ የሚያስችል የትምህርት ሥርዓት ሆነ አደረጃጀት አልነበረውም፡፡ ከእንግሊዝ ጋር የነበረው ስምምነት ከተቋረጠ በኋላ የአሜሪካ መንግስት ተራድኦ ድርጅት የኢትዮጵያን ትምህርት ሲደግፍ የነበረ ቢሆንም የዚህ ጊዜ ትምህርትም ቢሆን የእንግሊዝ ሥርዓተ ትምህርትን በመተው ወደ አሜሪካኖቹ በመቀየር ከአሜሪካ በመጡ መጽሐፍት የሚመራ ሥርዓተ ትምህርት ተዘረጋለት እንጂ አዲስ ነገር አላስገኘም፡፡ የኢትዮጵያ ትምህርት እንደ ጅምሩ ዕድገት እያሳየ የመጣ ሳይሆን መስመር የሚያሲዝለት ፖሊሲ ወይም ግልጽ የትምህርት አቅጣጫ

ሳይኖረው በጭፍን ሲጓዝ ዓመታትን አስቆጥሯል። በተለይ የተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባሕል ድርጅት ዩኔስኮ እ.ኤ.አ በ1960 በአዲስ አበባ ባካሄደው ዓለም አቀፍ የትምህርት ጉባኤ የኢትዮጵያ ትምህርት የሚጠበቅበትን ዕድገት ባለማሳየቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተችቶት እንደነበር ይታወሳል፡፡ በወቅቱ የሀገራችን ትምህርት ከአቅርቦት፣ ከሥርጭት፣ ከፍትሐዊነት፣ ከግብዓትና ከውጤት አንፃር ከአፍሪካ ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር በመጨረሻ ደረጃ ላይ ነበር።

የወቅቱ መንግስት ይህን ሁኔታ ለመቀየር አቅሙም ሆነ ፍላጎት ስላልነበረው ትምህርቱ በነበረበት ሁኔታ ቀጥሏል፡፡ ከሕዝብና ከዓለም አቀፍ ማሕበረሰብ በደረሰበት ጫና የንጉሱ ሥርዓት አዲስ የትምህርት አቅጣጫ ቀይሶ የነበረ ቢሆንም የሕዝብ ተሳትፎ ያልነበረው ወቅታዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘበና በድብቅ የተሠራ በመሆኑ ከፍተኛ ተቃውሞ አጋጥሞት ሳይተገበር ቀርቷል፡፡ በተለይ በንጉሱ መንግስት ላይ ለማመጽ እንደ አንድ ምክንያት የሚጠቀሰው ይኸው የትምህርት አቅጣጫ ነበር፡፡

ንጉሱ ከሥልጣን ከወረዱ በኋላ ሀገሪቱን ይገዛ የነበረው ደርግ ለትምህርትና ሥልጠና ግድ አልነበረውም። ትምህርት የሚመራበት ግልጽ ፖሊሲ ያልነበረው ሲሆን፣በወቅቱ ይታዩ የነበሩ የትምህርት ችግሮችን ለመፍታት ትምህርትን የዕድገትና የልማት መሣሪያ ለማድረግ ከቶም አልደፈረም ነበር። የደርግ መንግስት ሀገሪቱን በመራባቸው ዓመታት የነበረው ትምህርት በይዘቱ ሙሉ በሙሉ ከሶሻሊስት ሀገሮች የተቀዳ፣ የኮሚኒዝምን ጽንሰ ሀሳብ በማራገብ ላይ ያተኮረ ፖለቲካዊ ይዘት የተላበሰ የሕዝብን ፍላጎት ያላገናዘበ ትምህርት እንዲሰጥ አድርጓል፡፡

በተለይ የሕዝብ የትምህርት ፍላጎት እያየለ መምጣት ባሳደረበት ጫና ትምህርት በሶስት ፈረቃና በተጨናነቁ ክፍሎች እንዲሰጥ ማድረግን እንጂ ሕዝባዊ ፍላጎትን የሚያንፀባርቅ ለዕድገትና ለልማት የሚበጅ ፍትሐዊ የትምህርት አቅርቦት እንዲኖር ያደረገው ጥረት አልነበረም፡፡

## ከ1986 በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ ትምህርት ችግሮች

### 1. የአቅርቦትና ሥርጭት ውስንነት

በቀድሞ ዘመናት የነበረው የትምህርት አቅርቦት እጅግ ውስንና ለጥቂቶች ብቻ አገልግሎት ይሰጥ እንደነበረ ይታወቃል። ት/ቤቶች የተከፈቱት በትላልቅ ከተሞችና በከተሞች አካባቢ

ብቻ ስለነበር አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ልጆቹን ሰንቅ ቋጥሮ፣ በከተማ ቤት ተከራይቶ ማስተማር ካልቻለ ልጆቹ የትምህርት ዕድል አያገኙም ነበር፡፡

## 2. ሥርጭቱ ፍትሐዊ አለመሆን

በክልልና በክልል፣ በከተማና በገጠር፣ በሴቶችና በወንዶች እንዲሁም በብሔረሰቦች መካከል ከፍተኛ የትምህርት ተሳትፎ ልዩነት ይታይ ነበር። ለምሳሌ በአፋር፣ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ በሶማሌ ክልሎች በዋና ከተማ ከተገደቡ የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በላይ የትምህርት ዕድል አልነበረም። በሌሎች ክልሎችም አልፎ አልፎ በአውራጃ ደረጃ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከመኖሩ የዘለለ ትምህርት አልነበረም፡፡

## 3. የተገቢነት ማጣት

በቀደሙ መንግስታት ትምህርት ይሰጥ ነበር ቢባልም የሚሰጠው ትምህርት ከሀገር ተጨባጭ ሁኔታ፣ ከሕብረተሰብ የልማትና የዕድገት ፍላጎት ጋር የተገናዘበ ትምህርት አይሰጥም ነበር፡፡ በአብዛኛው በቀለም ትምህርት ላይ ብቻ ያተኮረ የተማሪውን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማምጣት ያላለመ፣ በሌሎች ሀገሮች ታሪክ ላይ የተመሠረተ ከራስ ይልቅ የውጭውን ዓለም የሚተርክ ትምህርት ነበር ይሰጥ የነበረው፡፡ ሥርዓተ ትምህርቶቹ ሙሉ በሙሉ ከውጭ ሀገር የተቀዱና የተገለበጡ ከመሆናቸው ሌላ በየጊዜው በሚወጡ መመሪያዎች ብቻ የሚመሩ ነበሩ፡፡ የመማር ማስተማር ዘዴው በቃል ነቢባዊነት ላይ ያተኮረ አስተማሪ ብቻ የሚናገርበት የተማሪው ተሳትፎ የማይታይበት የመማርን ውጤት ለመመዘን የማያስችል ነበር ፡፡

## 4. የጥራት ጉድለት

ለትምህርት ጥራት ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ዋነኛው የግብዓት መሟላት ነው፡፡ በቀደሙ ዘመናት የነበረው ትምህርት አስፈላጊ ግብዓቶች ሳይሟሉ የሚካሄድ ነበር፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱ በአብዛኛው በቀለም ትምህርት ላይ ያተኮረ፣ ለተግባራዊና ሙያዊ ትምህርት፣ የፈጠራ ችሎታን ለማዳበርና ክህሎትን ለማበልፀግ የሚያስችል አልነበረም። ተማሪዎች አካባቢያቸውንና ዓለምን በሚገባ ተረድተው የችግር ፈቺነት አቅም እንዲላበሱ የሚያስችል አልነበረም፡፡ የትምህርት አቀራረቡም የመማርን ፍላጎት የሚቀሰቅስ በተማሪው ዘንድም የትምህርት ፍቅርና ጉጉት የሚያሳድር አልነበረም፡፡ ከየትምህርት እርከኑ የሚወጣ ተማሪ ሊኖረው የሚገባ የእውቀት፣ የባሕርይ፣ የክህሎት በአጠቃላይም የአካል፣ የሥነልቦናና የማህበራዊ ኑሮ ተሳታፊነት ደረጃዎች ተለይተው የሚታወቁ አልነበሩም፡፡

በመምህራን በኩል ሲታይ ለመምህርነት ሙያ በቂ ዝግጅት ያላደረጉ ሌላ አማራጭ ያጡ የሚቀጠሩበት ሁኔታ እንጂ የሙያውን መስፈርት የሚያሟሉ የሚሠማሩበት ሁኔታ አልነበረም። ዕጩ መምህራን ከሥራ በፊት በቂ ሥልጠና የማያገኙ ሲሆን፣ ወደ ሥራ ዓለም ከገቡ በኋላም ቢሆን በሥራ ላይ የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና የማይሰጥ እንዲሁም ለሥራቸው ተመጣጣኝ ክፍያ የማያገኙበት ሁኔታ መኖሩ በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖም ሲያሳድር ቆይቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች ጥበት፣ የመቀመጫ ወንበር፣ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍት አቅርቦት፣ የቤተ መጽሐፍት አገልግሎት ዝቅተኛ መሆንም ለጥራት ላይ መጓደል ምክንያት ነበር፡፡

## 5. <u>የትምህርት ቋንቋ</u>

ሀገራችን ልሳነ ብዙ ሀገር በመሆኗ ወደ ት/ቤት የሚመጡ ሕፃናት ባንድ ቋንቋ ብቻ እንዲማሩ መደረጉ በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ተጽዕኖ ሲያሳድር ቆይቷል፡፡ ተማሪ በማያውቀው ቋንቋ እንዲማር በመገደዱም የትምህርቱን ጽንሰ ሀሳብ ለመረዳትና ሀሳቡን ለማስረዳት ከመቸገሩ በተጨማሪ ተማሪ በማንነቱና በቋንቋው እንዲያፍርና ትምህርት እንዲያቋርጥ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

## 6. <u>የትምህርት አመራር</u>

የትምህርት አደረጃጀትና አመራር እጅግ የተማከለ በቢሮክራሲ ውጣ ውረድ የተተበተበ ስለነበር የሕብረተሰብ ተሳትፎ የተገደበበት አዳዲስ ሀሳቦች የማይመነጩበት ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አካሄድ ይከተል ነበር፡፡

## 7. <u>የትምህርት ፋይናንስ</u>

አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ብሎም መላው ሕዝባችን የትምህርት ታክስና መሠል የትምህርት መዋጮ እንዲከፍል ይገደድ ነበር፡፡ ሆኖም እርሱ በከፈለው ታክስና መዋጮ የትምህርት ዕድል የሚያገኙትና የሚማሩት ጥቂቶች ነበሩ፡፡ የቀደሙ መንግስታት የትምህርት ሥርዓቱ የሚመራበት ግልጽ የትምህርት ፋይናንስ ፖሊሲ አልነበራቸውም፡፡

በአጠቃላይ የሀገሪቱ በጀት ለትምህርት የሚመድበው ከ9% ያነሰ ነበር፡፡ በተለይ ደርግ ያራምድ ከነበረው ጦረኛ ፖሊሲ የተነሳ ለትምህርት የሚመደብ ሀብት እጅግ ዝቅተኛ ነበር፡፡ ይህ ዝቅተኛ ሀብትም ቢሆን ቀልጣፋ፣ ግልጽነት የተላበሰና ሚዛናዊ ሥርጭትና አሠራር አልነበረውም፡፡

የግሉ ባለሀብት በትምህርት ዘርፍ የማይሳተፍበት ሕብረተሰብ በትምህርት ሥራ ድርሻ ያልነበረበት በልጆቹ የወደፊት ዕጣ ፈንታ በባለቤትነት የመምከርና ሀሳብ የማመንጨት መብት በእጅጉ የተገደበ አሠራር ሰፍኖ ነበር፡፡

## ድኅረ 1983 አዲስ የትምህርት ጉዞ

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ሲቀረጽ እነዚህንና ሌሎች በትምህርት ሥርዓቱ ይታዩ የነበሩ ከዘመን ዘመን ሲንከባለሉ የመጡ ውስብስብ ችግሮች ተፈትሸዋል፡፡

የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ችግሮች ተወግደው በአንፃሩ ትምህርት ለሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ልማት የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ የሚያስችሉ አማራጮች ሁሉ ተፈትሸዋል፡፡

በየደረጃው ልዩ ልዩ ጥናቶችና ምርምሮች ተካሂደው ከባለሙያዎች፣ ከባለድርሻ አካላትና ከሕብረተሰብ ጋር ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡ በውይይቶች ግኝትም የነበሩብንን የትምህርት ሥርዓት ችግሮች ባጭር ጊዜ በመፍታት ቀጣይነት ያለው ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች ተነድፈው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

ከ1987 ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እነዚህን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ፈትሾ መፍትሔ ያስቀመጠ ከመሆኑም በላይ ለአፈጻጸም የሚያግዝ ስትራቴጂና የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች ተቀርጸው ሥራ ላይ ውለዋል።

## በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በመመራት በተከናወኑ ተግባራት የተመዘገቡ ውጤቶች

በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በፖሊሲው መሠረት በተዘጋጁ ስትራተጂና የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች በመመራት በተካናወኑ ተግባራት ዓለም አቀፍ አድናቆት የተቸራቸው ውጤቶች ተመዝግበዋል። ከሁሉም በላይ እጅግ የሚደንቀው እጅግ ዝቅተኛና በአደገኛ ውድቀት ላይ የነበረውን የትምህርት ሥርዓት መልሶ በማደራጀት ባጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ መቻሉ ነው። ይህም መንግስታችን የሚከተለው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ትክክለኛና አማራጭ የማይቀርብለት መሆኑን ያረጋግጣል።

## 1. የትምህርት ተሳትፎን ማሳደግ

### የአጸደ ህጻናት ትምህርት

ህጻናትን ለመደበኛ ትምህርት በባህሪይም ሆነ በአካዳሚያዊ ችሎታቸው ለማሳደግ የአጸደ ህጻናት (የቅድመ መደበኛ) ትምህርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። የአጸደ ህጻናት ትምህርት ከማግኘት ቀጥሎ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች ለሚቀስሙት ክህሎትና እውቀት እንዲሁም አመለካከት ብቻ ሳይሆን የትምህርት ማቋረጥን ለመቀነስና ለሚፈለገው ደረጃ ለማብቃት አስፈላጊ ነው።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ጠቃሚነት ላይ ግንዛቤ ቢኖርም በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያሳየው እድገት እና የማስፋፋት መጠን አዝጋሚም ቢሆንም በየጊዜው ለውጥ እየታየበት ሄዷል፡፡ በዝሁ መሰረት በ2002 ዓ.ም ተሳትፎው ወንድ 175,576; ሴት 165,738 በጠቅላላ 341,315 ሕጻናት በ3,318 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል፡፡

ከሀገራችን የህዝብ ዕድገት አንጻር የአጸደ ህጻናት መስፋፋትን ስንመለከት አዝጋሚ የመሆኑ ምክንያት በዋናነት መንግስት ባለው ውስን አቅም በ1ኛ ደረጃ ትምህርት ማስፋፋት ላይ በማተኮሩ፤ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ለግል ባለሀብቶች (private sector) መተውና ልጆቹን ከፍሎ ለማስተማር አቅም ላለው ለህብረተሰባችን ክፍል ብቻ አገልግሎት መሰጠቱ አብዛኛውን ህጻናት ቅድመ መደበኛ ትምህርት ሳያገኙ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት እንዲገቡ አድርጓቸዋል።

በተከታታይ በተመዘገበው የኢኮኖሚ እድገት ምክንያት በገጠሩ የሀገራችን ክፍል ክፍያውን መፈጸም የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር እየጨመረ ቢመጣም የአጸደ ህጻናት ስርጭት በከተሞች ብቻ የተወሰነ መሆኑና የገጠሩ ህጻናት ይህንን እድል አለማግኘታቸው ቀጥሎ ባለው የመደበኛ ትምህርት ስኬታቸው ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን በአንዳንድ ክልሎች የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

የአጸደ ህጻናት ትምህርት አለመከታተል በመጀመሪያ ደረጃ 1ኛ ሳይክል ተማሪዎች ሊያሟሉ የሚገባቸውን የማንበብ፤ የመጻፍና አካባቢያቸውን ከትምህርቱ ጋር በማቆራኘት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የመመልከት ክህሎታቸው ዝቅ እንዲልና ፕሮፋይሉን እንዳያሟሉ ያደርጋል።

ስለሆነም በገጠሩ የሀገራችን ክፍል የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ለማስፋፋት በአንድ በኩል የግል አጸደ ህጻናት እንዲስፋፉ በማበረታታት፤ በሌላ በኩል ህብረተሰቡ በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸውና የሚከታተላቸው የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን በመመስረት ማሳተፍና ችግሮቹንም ለመፍታት መንግስት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ስርአተ ትምህርት፣ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና የአተገባበር መምሪያ አዘጋጅቷል።

## የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት

በ1986 ዓ.ም በተቀረፀው ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ አማካይነት በሀገራችን ዘመናዊ ትምህርት በመቶ አመት ዕድሜው በውስብስብ ችግሮች ተተብትቦ በዳዴ ይጓዝበት የነበረበት ሁኔታ መፍትሄ እንዲያገኝ ተደርጓል። ባለፉት ጥቂት አመታት በተነደፉ ስትራቴጂዎችና የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሀ ግብሮች እንዲሁም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው በፈጠረው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ህዝቡ በትምህርት ማስፋፋት ስራ ላይ በሰፊው መሳተፍ በመጀመሩ የትምህርት ተደራሽነትን በማረጋገጥ ረገድ አበረታች ውጤት ተገኝቷል። ለአብነት ያህል በ1983 ዓ.ም በ1ኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ 19.6% (ወንድ 22%; ሴት 16%) የተማሪዎች ቁጥር ወንድ 1,200,393፣ ሴት 863,242 ድምር 2,063,635 የነበረው በ2002 ዓ.ም. መረጃ መሰረት ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ 93.4% (ወንድ 96.6%; ሴት 90.1%)፣ የተማሪዎች ቁጥር ወንድ 8,309,889፣ ሴት 7,482,215 ድምር 15,792,104 ደርሷል። የትምህርት ቤቶች ቁጥርም በተመሳሳይ ጊዜ 8,434 የነበረው በ2002 ዓ.ም ወደ 26,951 አድጓል።

ፍትሃዊነትን ከማረጋገጥ አንፃር በገጠርና በከተማ፣ በክልልና በክልል፣ በሴቶችና በወንዶች እንዲሁም በብሄረሰቦች መካከል የነበረው የተዛባ የትምህርት ስርጭት ሁኔታ እንዲስተካከልና ፍትሃዊ እንዲሆን በተሰራው ስራ ቀድሞ እጅግ ሰፊ የነበረው ልዩነት በሁሉም ረገድ በአሁኑ ጊዜ በአንጻራዊነት ሊጠብ ችሏል።ህብረተሰቡም ለትምህርት ያለው አመለካከት በተለይም የገጠሩና አርብቶ አደሩ አዎንታዊ በሆነ መልክ እንዲቀየር በመንግስት በኩል በተደረጉ ጥረቶች ለትምህርት የሚሰጠው ትኩረት ከፍ እያለ በመምጣቱ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ለማድረግ የራሱ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው፡፡ በዝህም በ2002 ዓ.ም የተማሪዎች አመታዊ የዕድገት ምጣኔ 6% ሊሆን ችሏል፡፡ ንጥር ተሳትፎንም በተመለከተ 82.1%(ወንድ 83.7%; ሴት 80.5%) ሆኖዋል፡፡ በክልሎች መካከል ስለተመዘገበው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎም አብዛኞቹ ክልሎች ከተቀመጠላቸው የጥቅል ተሳትፎ ግብ አኳያ

በጥሩ ሁኔታ ላይ አሉ፡፡ በተለይ በአፋርና በሶማሌ ክልሎች በሦስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የመጨረሻ አመታት የተመዘገበው ተሳትፎ አበረታች ሲሆን አገራችን የሚሊኒየም ግቡን ማሳካት እንደምትችል አመላካች ነው፡፡ በ2002 ዓ.ም የአፋርና የሶማሌ ክልሎች ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ በቅደም ተከተል 58.2% እና 70% ደርሷል፡፡ አዲስ ከተገነቡት ትምህርት ቤቶች 85% የተሰሩት በገጠሪቱ የሀገሪቱ ክፍል መሆኑን ስንመለከት ከዚህ አኳያ የተሰራው ስራ ከፍተኛ መሆኑን ማየት ይቻላል፡
፡

## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

መንግሥት ለ1ኛ ደረጃ ትምህርት መስፋፋት ቅድሚያ እየሰጠ ባለበት ሁኔታ የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን ለማስፋፋት ካስቀመጥነው አቅጣጫና ግብ አንፃር ሲገመገም አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል። በተለይም በ3ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ትኩረት በመስጠት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎን ለማሳደግ ግብዓት ከማሟላት ጭምር በመሰራቱ በገጠርና በሁሉም አካባቢዎች በርካታ ት/ቤቶች ተከፍተዋል፡፡

በመሆኑም በ1998 ዓ.ም 835 የነበሩት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች(9-12) በ2002 ዓ.ም 1,335 ደርሰዋል፡፡ በዚሁ ወቅት(ከ9ኛ-12ኛ) የመምህራን ቁጥርም ወደ 46,060 አድጓል። በከተማና ገጠር መካከል የነበረው የተሳትፎ መጠን ልዩነት የከተማውን የተሳትፎ ዕድገት ሳይገድብ ዝቅ ብሏል፡፡

የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዝ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ስትራቴጂም ተዘጋጅቷል፡፡ በስትራቴጂው መሰረት የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-10) በ2012 ዓ.ም ዕድሜያቸው ለደረጃው ለሚመጥኑ ዜጎች የማዳረስ ግብ ተቀምጧል፡፡ ይህ ግብ ተገቢ ግን ደግሞ ፈታኝ ነው፡፡

በዝህ መሠረት በ2002 ዓ.ም የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ወንድ 818,280 ፣ ሴት 634,570 ድምር 1,452,850፤ ጥቅል ተሳትፎ 39.1 % (ወንድ 43.5 %; ሴት 34.7%) ሲደርስ በከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ (11ኛ -12ኛ ክፍሎች) ወንድ 156,194፣ ሴት 86,886 በድምሩ 243,080 ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተዋል።

የ2ኛ ደረጃ ትምህርት በዘፈቀደ የሚስፋፋ ሳይሆን የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሁኔታ ከሚፈልገው መካከለኛና ከፍተኛ ባለሙያዎችን ከማፍራት ፍላጎት አንጻር በእቅድ የሚተገበር መሆን አለበት። አፈጻጸሙም 80% የሚሆኑ ተማሪዎችን

ለመካከለኛ ሙያተኝነት ወደ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ 20% የሚሆኑት ደግሞ ወደ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚገቡና ለከፍተኛ ትምህርት የሚዘጋጁ መሆናቸውን ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 2. የትምህርት ስርጭት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ

በከተማና በገጠሩ፣ በሴትና በወንድ፣ በአርሶአደሩና አርብቶአደሩ፣ በብሔረሰቦች መካከል የትምህርት ዕድል ያላገኙ ግለሰቦች ትምህርትን በፍትሃዊነት እንዲያገኙ ከማድረግ አንጻር በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መሠረት በከተማና በገጠር አዲስ ከተገነቡት ት/ቤቶች ውስጥ 85% በገጠር ነው፡፡በሴትና በወንድ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ የሴቶች ትምህርት ስትራቴጅክ ሰነድ በ1997 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል።የሴቶች ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ በ2002 ዓ.ም በአንደኛ ደረጃ(ከ1ኛ-8ኛ) 90.1%፣ በሁለተኛ ደረጃ(ከ9ኛ-10ኛ) 34.7%፣ (ከ11ኛ-12ኛ) 5.0% ሆኗል፡፡ በአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ-አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት(ABE) በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢ እንዲሰጥ በማድረግ ተጨባጭ ለውጥ እየተመዘገበ ይገኛል፡፡ በ2002 ዓ.ም 955,694(ወ 531,203; ሴ 424,491) ተማሪዎች ትምህርታቸውን በዚህ ዘርፍ እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡ ነባር ብሄረሰቦችን የትምህርት ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በፊት የትምህርት ዕድል ያላገኙ ግለሰቦች የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጅ ተነድፎ በ6 ሚኒስቴር መሣሪያ ቤቶች የመግባቢያ ሠነድ ተፈርሞ እንዲሁም የተለያዩ የማስፈጸሚያ ሰነዶች ተዘጋጅተው እየተሰራበት ይገኛል፡፡

## 3. የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጥ

በዘመናዊ ሕብረተሰብ ማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ ጉልተው ከሚታዩት ተግባራት መካከል ትምህርትና ሥልጠና ዋናዎቹ ናቸው ተብለው ይታመናሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ሕዝቦችና መንግስታት ለትምህርትና ሥልጠና ዓላማ መሳካት የሚቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ስለትምህርትና ሥልጠና ጥራትና ብቃትም በእጅጉ ያስባሉ፡፡ ሀገራችንም ከዚህ እውነታ ውጭ አትሆንም፡፡ ዛሬ በሀገራችን በትምህርት በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት የተሳካልን ቢሆንም የትምህርት ጥራት በማስጠበቁ ሥራ ብዙ ይቀረናል፡፡ በመሆኑም የተጀመሩትን ሥራዎች አጠናክሮና አስፍቶ መሄድን ይሻል የትምህርት ጥራትንም ከትምህርት ማስፋፋት ጐን ለጐን ማከናወንም ይገባል፡፡ ይህንን ሥራ በሚገባ ለማከናወን ግን ከመነሻው የትምህርት ጥራት ምንነት፣ በትምህርት ጥራት ተፅዕኖ የሚያደርሱ ጉዳዮችና አስፈላጊነትን አንጥሮና ተግባብቶ ጉዞ መጀመር ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህም በበኩሉ

ባለድርሻዎችን ሁሉም በአንድ አውድ ላይ በማሰባሰብ ከያንዳንዱ ባለድርሻ የሚጠበቅ ኃላፊነትና አስተዋጽኦ በመረዳት ወደ ሥራ በመግባት ለትምህርት የተቀመጡ ግቦችን በሚፈለገው ደረጃ ማሳካት ያስችላል፡፡

## 1. <u>የትምህርት ጥራት ጽንሰ ሃሳብ</u>

የትምህርት ጥራት ጽንሰ ሃሳብ ውስብስብ ከመሆኑ የተነሣ ወጥና ሁሉን ወገን በሚያስማማ መልኩ ለመግለጽ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

አንዳንድ ምሁራን የትምህርት ጥራትን በሚመለከት ሦስት ተያያዥነት እና ተደጋጋፊነት ያላቸውን መግለጫዎች እንዳሉት ያስቀምጣሉ፡፡

- ለትምህርቱ የተቀመጡ ግቦችን የማሳካት ብቃት፣
- ትምህርቱ የሕብረተሰቡና የአካባቢው ፍላጎቶችን ለማሟላት ያለው ብቃትና ተገቢነት እና
- የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ለማዳበርና አዳዲስ ነገሮችን ለማጥናት የሚያበረታታ ሆኖ መገኘት ናቸው፡፡

ሌሎች ምሁራን ደግሞ ከላይ የተገለፁት /የተዘረዘሩት ነጥቦች ተቀባይነት ቢኖራቸውም ትምህርት በቴክኒካዊ ብቃት (Technical efficiency) ይገልጹታል፡፡ የትምህርት ጥራት በቴክኒካዊ ብቃት የሚገልፁት መሠረታዊ የሆኑ የትምህርት ቤት አቅርቦቶች (Basic School inputs) መሟላት፣ ለምሣሌ በቂና ብቃት ያላቸው መምህራን የትምህርት መሣሪያዎች የትምህርት ጊዜ ሽፋን መሟላትና የነዚህ አቅርቦቶች በተማሪዎች የትምህርት ውጤት እና በአካባቢው ልማት ላይ በሚኖረው አዎንታዊ ተጽዕኖ ደረጃ ላይ ነው ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ምሁራን የትምህርት ጥራትን ፔዳጎጂካዊ ገጽታው የሚተረጉሙም አሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን ለትምህርት ቤት አቅርቦቶችና ውጤታቸው ለሚያመጡት አዎንታዊ ተፅዕኖ ቢቀበሉም የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ግን ለማስተማር ክህሎቶች ለትምህርት ቤት አደረጃጀት ለሥርዓተ ትምህርቱ ይዘት ነው:: እነዚህ ምሁራን የትምህርት ጥራት በዋነኛነት የሚረጋገጠው በነዚህ ተፈላጊ ፔዳጎጂካዊ ክፍሎች (Components) መሟላት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት በተለያዩ ምሁራን የተገለፁት የትምህርት ጥራት ትርጉም መገለጫዎች የአስፈላጊነታቸው ደረጃ ይለያይ እንጂ ለጥራት የሚያስፈልጉ ባህርያት ናቸው፡፡ ለአንዳንዶቹ ምሁራን ለተወሰኑት መገለጫዎች በአንፃራዊነት ክብደት የመስጠት ጉዳይ

እንጂ ጨርሶ እንደማያስፈልጉ መከራከሪያ አያቀርቡም:: ይህም ሆኖ ግን ለትምህርት ጥራት የሚሰጠው ትርጉም ይለያያል፡፡ ለመለያየቱ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የህብረተሰቡ እሴትና የእድገት ደረጃ ጥቂቶቹ ነጥቦች ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ የትምህርት ጥራት ትርጓሜና ግንዛቤ ከግብአትና ከውጤት ጋር የተያያዘ ሲሆን እነዚህም የሕብረተሰቡ አጠቃላይ እሴት (Value) እና በዕድገት ደረጃቸው የሚገለጽ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የትምህርት ጥራትን እውን ከማድረግ አንፃር ብዙ ጉዳዮችን ታሣቢ ማድረግ እንደሚገባ ምሁራን ያሳስባሉ፡፡ ዛሬ ዓለማችን በደረሰችበት የቴክኖሎጂና የልማት ዕድገት አንፃር የትምህርት ጥራት የአንድ ተቋም ብቸኛ ኃላፊነት ሳይሆን የሁሉም ወገኖች (Stakeholders) ድምር ውጤት መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ ለዚህም መንግሥት፣ መምህራን ፣ የትምህርት ቤት አመራሮች፣ ወላጆች ወዘተ ሌሎችም የሚመለከታቸው ሁሉ የየድርሻቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

በመሆኑም የመንግስት ጥረቶች በሚከተሉት ተግባሮች መደገፍ ይገባቸዋል፡፡ እነሱም ትክክለኛ ፖሊሲ በመቅረጽ፣ ተገቢውን እቅድ በማዘጋጀትና በመተግበር፣ በትምህርት አመራርና ትክክለኛና ወቅታዊ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት ወዘተ ሲሆን መምህራን ደግሞ የሚያስተምሩትን ትምህርት በሚገባ በማወቅና በሥነ ትምህርት ክህሎት በመዘጋጀት ተገቢውን ሥነ ምግባርና ባህሪ በመጨበጥ ዝግጁ መሆን፣ ወላጆች የልጆቻቸውን ትምህርት በመከታተልና በመደገፍ ርዕሰ መምህራን በትምህርት ቤት ለአመራር ብቃታቸው ወዘተ ተቀናጅተው መንቀሳቀስ እውነተኛ የትምህርት ጥራትና ፍላጎት እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡ በመሆኑም ከላይ ከቀረቡ ሃሳቦች የምንረዳው ዋነኛ ቁም ነገር የትምህርት ጥራት ለማስጠበቅ የሚቻለው በአንድ ብቸኛ ተቋም ሳይሆን የተቀናጀና የጋራ ሥራን (Partnership) የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡

ሌላው ቁምነገር የምንረዳው የትምህርት ጥራት ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች እንደሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታና የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ዕድገት ደረጃ ሊወሰኑ እንደሚችሉ ነው፡፡ ሆኖም ግን በአብዛኛው ሀገሮችና ምሁራን ተቀባይነት ያገኙ የትምህርት ጥራት መስፈርቶች አሉ እነዚህም፡-

- ከማንኛውም አድሎና አመለካከት የፀዳ፣ የሀገርንና የሕዝብ ሁኔታ ያገናዘበና አለም አቀፍ ስታንደርዱን የጠበቀ ሥርዓተ ትምህርት መምህሩ እየመራው ተማሪ ተኮር የሆነ የማስተማር ዘዴን የሚያበረታታ፣
- ሙያዊ ሥነምግባር የተላበሱ የሚያስተምሩትን ትምህርት በሚገባ የሚያውቁና ሙያዊ ብቃት ያላቸውንና ይህንኑ በተግባር ሊያውሉ የሚችሉ መምህራን፣

- ቀልጣፋና ብቃት ያለው የትምህርት አደረጃጀትና አመራር ሥርዓት እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ያለው፣
- ጥራት ያላቸው አስፈላጊና አግባብነት ያላቸው የትምህርት መማሪያዎችና አቅርቦት መሟላት፣
- ምቹ ጤናማ፣ ማራኪ የሆኑ የመማሪያ ክፍሎችና የትምህርት ቤት አካባቢ (Safe, Secure School Environment)
- በቂ የትምህርት ጊዜ ሽፋን በቋንቋ፣ በሂሳብና በሂሣብ ትምህርቶች የሚሰጡባቸው ሆኖ ሁሉም ማለት ይቻላል በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን የሚስማሙበት ሃሳብ የትምህርት ጥራት የሚወሰነው ለትምህርቱ የታለመው ግብ ምን ያህል ተፈፃሚ እንደሆነ (fit to the purpose) በሚገኘው ውጤት ነው፡፡

በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩት የጥራት መስፈርቶች በመጨረሻ የሚለኩት በሚገኘው የተማሪዎች ውጤት እና ተማሪዎች በማህበራዊ ኑሮ፣ በኢኮኖሚው እና በፖለቲካው ተሣትፈው በሚያስገኙት ስኬት ነው፡፡

በመሆኑም የሚሰጠው ትምህርት ከሕብተረሰቡ ፍላጎትና የእድገት ደረጃ ጋር መገናዘቡን ከአለም አቀፍ ሁኔታዎችና አዳዲስ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ጋር አብሮ ሊጓዝ የሚችል መሆኑን በየጊዜው እያረጋገጡ ወቅታዊነትን ጠብቆ እንዲሰጥ ማድረግ ለትምህርት ጥራት እውን መሆን የማይታለፍ ተግባር ነው፡፡

## 2. <u>የትምህርት ጥራት ለማምጣትና ተገቢነትን ለማረጋገጥ የተመረጡ ስልቶችና ስትራቴጂዎች</u>

ስርጭት ማስፋፋትና ተሣትፎ ማሣደግ ጋር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ የትምህርት ጥራትና ተገቢነት በተሻለ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ማድረግ ነው፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅም በሁሉም ዘርፍ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ውጤት ለማስመስገብ የተንቀሳቀስን ብንሆንም ከሚፈለገው የጥራት ደረጃ ላይ ለመድረስ ግን ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት 1999 ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት ሚኒስቴር መጠነ ሰፊ ጥናት ክልሎችና የፌዴራል ባለሙያዎችን በማካተት በመላው ሀገሪቱ በማካሄድ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፖኬጅ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡

ይህ የጥራት ማረጋገጫ ፖኬጅ ስድስት ፕሮግራሞችን በመያዝ የተደራጀ ሰነድ ነው፡፡ እነሱም፡-

1. የመምህራን ልማት መርሃ ግብር፣

2. የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃ ግብር፣
3. የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ መርሃ ግብር፣
4. የሥነዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት መርሃ ግብር፣
5. የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት መርሃ ግብርና
6. የትምህርት ዘርፍ አመራር ከፌዴራል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ የሚሉ ናቸው፡፡

እነኚህን መርሀ ግብሮች ለማስፈፀም ጥናቶች፣ ገዥ መመሪያዎች፣ ስታንደርዶች መጽሐፍ እዶች (hand books) የተዘጋጀው የትምህርት ቤት አመራሩን መምህራንና በወረዳ ደረጃ የፖለቲካ አመራሩን በማሰልጠን ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ እያንዳንዱን ሰነድ አግባብ ያላቸው ባለድርሻዎች ትርጉም ባለው መልኩ ተወያይተውባቸው በግብረ መልሶች ከዳበሩ በኋላ ታትመው ተሰራጭተዋል፡፡ ዛሬ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የትምህርት ቤት ማሻሻያ ስትራቴጂክ እቅድ በመንደፍ የተማሪዎችን ውጤትና ሥነ ምግባር ለማሳደግ ቤተሰብን፣ መምህራንና ተማሪዎችን በማሳተፍ ግብ ተይዞ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ዛሬ ተማሪዎችን ከጎረቤትና ከአለም አቀፍ ከሌሎች ሀገሮች ተማሪዎች ጋር የሚያወዳድረን መሰረታዊ የሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎችን በመቅረጽ ሳቢና ደረጃውን የጠበቀ መጽሐፍቶች እንድዘጋጁ ተደርገዋል፡፡ ይህም አፈፃፀም በዓለም አቀፍ ጨረታ በማውጣት የተዘጋጀ ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ አድሶቹ መጽሐፍቶች እስከ 2003 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ሙሉ በሙሉ በተማሪዎች እጅ የሚደረስ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ መጽሐፍቶች ደግሞ በ2004 ዓ.ም ለተማሪዎች ይሰራጫሉ፡፡ ለአንድ ተማሪ አንድ መጽሐፍ እንዲዳረስ በማቀድ የሥርዐተ ትምህርት ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህም በመነሣት የሣይንስና የሒሣብ ትምህርቶች እንደዋነኛ ትምህርት እንዲሆኑ ስትራቴጂ ቀርፀን ወደ ሥራ ገብተናል፡፡

ዛሬ መምህራኖቻችን በፍላጎት፣ በዝንባሌ፣ በሥነምግባራቸው እንዲሁም ቀደም ብለው ባስመዘገቡት የትምህርት ውጤት ተመልምለው፣ በሚያስተምሩት ትምህርት ሆነ ትምህርቱን ማስተላለፍ በሚያስፈልጋቸው ሙያዊ ዕውቀትና ክህሎት የሚሰለጥኑበት ሥርዓት ዘርግተን ወደ እንቅስቃሴ ገብተናል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የመምህራን ምልመላ፣ ቅድመ ሥራ ሥልጠና፣ የሥራ ምደባ እና የማያቋርጥ ተከታታይ የሆነ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናን ያካትታል፡፡ ዕጩ መምህራን ወደ መምህርነት ሙያ ከመግባታቸው በፊት ፈቃድ እንዲያገኙና በሥራ ሂደትም የሙያ ፍቃዳቸውን እያሳደሱ የሚሄዱበት ሥርዓት በዝርዝር የተለያዩ ሀገራት መልካም ተሞክሮዎችን በማካተት ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ ይገኛል፡፡ ባለድርሻዎችን

በማወያየት ግብረ መልስ በማሰባሰብ የመጨረሻ ቅርፅ በማስያዝ ወደ ተግባር የሚገባ ይሆናል፡፡

የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር አስተሳሰብ በወጣቱ ትውልድ እንዲሰረጽና የበላይነት እንዲያገኝ በማድረግ በሀገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ለማስቻል ከሕገ መንግስታችን በመነሣት የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት መርሃ ግብር ተቀርፆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህ መርሃ ግብር መሠረትም ተማሪዎቻችን በሳይንሳዊ አስተሳሰብ የተገነቡና የሚመሩ ኋላቀርና ጎታች አስተሳሰቦችን የማይሸከሙ፣ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ውሣኔ ላይ የሚደርሱ፣ ለእውነት ተገዥ የሆኑ ዜጋ ሆነው እንዲፈሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለን እናምናለን፡፡

በሌላ በኩል ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ጥራት ያለው ትምህርት ለማስፋፋት፣ የመምህራንና የትምህርት አመራርን አቅም የአሠራር ሥርዓት ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ እና የተማሪውን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕውቀት ክህሎት ለማሳደግ በሥርዓተ ትምህርቱ በማካተት በቴክኖሊጂው ብቃት ያለውና ተወዳዳሪ ዜጋ ለመፍጠር እንቅስቃሴ ውስጥ እንገኛለን፡፡ ከላይ የገለጽናቸው ተግባራት በተግባር ተተግብረው ውጤታማ ለማድረግ ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት ድረስ በተዋረድ የሚፈሱት ተግባራትና እንቅስቃሴዎች በተፈለገው ፍጥነት፣ እና ትኩረት ተጉዘው በትምህርት ቤት ደረጃ የሚካሄደውን የመማር ማስተማር ተግባራትና እንቅስቃሴዎች ሊያሳልጡ ይገባል፡፡ በዝህም መሠረት ለክልሎች የፕላዝማ ቴሌቪዥን ግዥ ተከናውኗል፡፡ በነባሩ ሥርዓተ ትምህርት መሠረት በዘጠኝ የትምህርት ዓይነቶች ላይ የተዘጋጁት የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች በ12 የሳተላይት ቴሌቪዥን ቻናሎች እየተሰራጩ የቆዩ ሲሆን በተሻሻለው ሥርዓተ ትምህርት በ12ቱ የትምህርት ዓይነቶች ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሳተላይት ቴሌቭዥን ትምህርት ፕሮግራሞችን ጥናት በማድረግ ለማሰራጨት ሙከራ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህንን በአስተማማኝ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው ደግሞ የትምህርቱን ሥራ በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የአመራር፣ የአሠራርና የአደረጃጀት ሥርዓት ሲዘረጋ ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፋችን መልካም አስተዳደር፣ ያልተማከለ ሥርዓት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት ዲሞክራሲያዊ አሠራር፣ ሥልታዊ አመራር መስጠት የሚችሉ ቁርጠኛና ብቃት ያላቸው አመራሮች ወደ ሥራ ለማስገባት እና ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ የሆነ አመራርና አሠራር ለመፍጠር የሚያስችል ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡ ለዝህም የሚያግዝ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም በአንዳንድ ት/ቤቶች የተማሪዎች ዲሲፕሊንና ውጤት መሻሻል አሳይቷል፡፡ እንደዚሁም የተማሪዎች የትምህርት ሰዓት

ማክበርና በአግባቡ መከታተል ተሻሽሏል፡፡ በሌላ በኩል ሦስተኛው የትምህርት ልማት መርሃግብር (ESDP III) መሠረት በማድረግ ለትምህርት ጥራት አስተዋጽኦ የሚያበርክቱ ግብአቶችን ለማሟላት ግብ በማስቀመጥና ለተግባራዊነቱ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከነዚህ ግቦች የተማሪ መምህር ጥምርታ፣ የተማሪ ክፍል ጥምርታ፣ መፃሕፍት ለሁሉ ተማሪ አንድ አንድ እንዲዳረስ ማድረግ፣ በየትምህርት ቤቱ በቂ የላቦራቶሪ ክፍሎችና መሣሪያዎችን ማሟላት እና ቤተ-መፃሕፍትን ማሟላት ይገኙበታል፡፡ በዚህም በየጊዜው ውጤት እየተገኘ እንደሆነ የክልሎች ሪፖርት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ከላይ በአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ የታቀፉ መርሃ-ግብሮችና ትግበራቸው ዓለም አቀፍ ምሁራንና ተቋማት (UNESCO, UNICEF) የትምህርት ጥራት መለኪያ መስፈርት ከተስማሙባቸው ጋር በጣሙን የተቀራረበና ሁሉንም መስፈርቶች ያካተተ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በቀረጽነውና ወደ ትግበራ በገባንበት ፓኬጅ መሠረት የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ እንደሚቻል ሙሉ እምነት አለን፡፡ የእኛ እምነት ብቻም ሳይሆን ዓለም አቀፍ ተቋሞችና የልማት አጋሮቻችን ጭምር የትምህርት ጥራት ለማስገኘት የዘረጋነው እቅድና ፓኬጅ በቀጥታ በመደገፍ ለትግበራው በሀብት ጭምር እያገዙን ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ዓለም ባንክ፣ FTI, የፊንላንድ፣ የሲዉድን የጣልያን፣ የእንግሊዝና የኔዘርላንድ መንግስታት በብድር ሀምሣ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በዓለም ባንክ በኩል፣ ሌሎቹ ከላይ የተጠቀሱ ሀገራት እና ፋስት ትራክ ኢኒሼቲቭ (Fast-Track-Initiative) ተቋም በዓለም ባንክ በኩል እስከ መቶ ሰማንያ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለአራት አመት ድጋፍ ሰጥተውናል፡፡ በቀጣይም የአምስት ዓመት የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም(ESDP IV) በማዘጋጀት ተግባር ውስጥ ገብተናል፡፡

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ጥረቶች ሁሉም ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን በንቃት፣ በቅንነት ሊወጡ ይገባል፡፡

ስለትምህርት ጥራት ስንናገር በእጅጉ ማሰብ የሚገባን ተማሪዎች ከየትምህርት እርከኑ ትምህርታቸውን ጨርሰው በምስክር ወረቀቶችና በማዕረግ መመረቃቸው ብቻ ሳይሆን የዛሬውና የመጪውን አገርና ዓለም በግንባር ቀደምነት በህብረት ለመገንባት እንዲችሉ የአብሮ መኖር ትምህርት /የመቻቻል፣ የመተባበር፣ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ከኃይል ጥቃት (Violence) የመቆጠብና ሌሎች የሕይወት ክህሎት (Life Skills) እንዲሁም መሠረታዊ የህይወት ክሂሎት በአግባቡ ስለመቅሰማቸው ወይም አለመቅሰማቸው ሊሆን ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በዛሬው ዘመን የትምህርት ማዕቀፍ ይበልጥ ደግመን ደጋግመን ማሰብ የሚኖርብን ተማሪዎች አብሮ መኖር የሚያስችላቸውን ትምህርት መማር መቻላቸው፣

ፍትሐዊና ሁሉንም ዜጋ የሚያቅፍ የትምህርት ሥርዓት (Inclusive) መዘርጋቱን፣ በየጊዜው ከሚለዋወጠው የሕብረተሰብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ ፍላጎት ጋር መጣጣም የሚችል የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራም መቅረጽን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች ውጭ የምናስበው የትምህርት ጥራት የለምና፡፡ ስለዚህ የትምህርት ጥራት በአንድ ጀምበር የሚገኝና የሚፈፀም አይደለም፡፡ የአንድ ተቋም ወይም ተቋማት ጥረት ብቻ ሳይሆን የሁሉንም ባለድርሻዎች ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚጠይቅ ውስብስብ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሁላችንም አሁን የዓለም አቀፍና የሀገራችንን ተሞክሮ በመቀመር የትምህርት ጥራት ለማምጣት የተዘረጉ ፓኬጆች፣ ስትራቴጂዎችና እቅዶች በጋራ ተባብረን እንተግብራቸው፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎቻችንና ሠልጣኞቻችን ትምህርትና ሥልጠና ከአጠናቀቁ በኋላ በሚጨብጡ እውቀት፣ ክህሎት፣ባህሪና እነዚህም እውቀቶች፣ ክህሎትና ባህሪ በመጠቀም ሀገሪቱ በትምህርት አሳካዋለሁ ብላ ከአስቀመጠቻቸው ግቦችና በሕብረተሰቡ አዎንታዊ ተሣትፎ ስኬት አኳያ የትምህርት ጥራታችንን በየጊዜው በነፃ አካላት መንግስትና ባለሙያ የምንለካው ይሆናል፡፡ በርግጠኝነት የምንናገረው ነገር ቢኖር በሀገራችን የትምህርት ጥራት ችግር እንዳለና መንግስትም ይህንን ችግር በመለየት መፍትሔ አስቀምጦ እርምጃ መውሰድ መጀመሩን ነው፤ የተወሰደውም የመፍትሄ እርምጃ ውጤት እንደሚያስገኝ በርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

## የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ አፈጻጸም

ባለንበት ዘመን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘትና ለሀገር ኢኮኖሚና ልማት ተገቢውን ሃላፊነትና ድርሻ ለመወጣት ወሳኝ የሆነው ግብአት ትምህርትና ስልጠና በመሆኑ የተለያዩ ሀገሮችና መንግስታት ለዚህ ሴክተር ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው በመስራት ላይ ይገኛሉ። ስለትምህርትና ሥልጠና ጥራትና ብቃትም በእጅጉ ያስባሉ። በሀገራችንም የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ለማሻሻል በሚደርገው ጥረት መልካም ጅምሮች እየታዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን መልካም ጅምሮች አጠናክሮና አስፋቶ መሄድ እና የትምህርት ጥራትንም ከትምህርት ማስፋፋት ጐን ለጐን ማረጋገጥ ይገባል። በሀገራችን የትምህርት ጥራት የትኩረት አቅጣጫ የሆነዉ ከላይ ከተገለጸው ምክንያት በተጨማሪ ለዚህ የሚገፋፉ በርካታ ምክንያቶችም ስላሉ ነው፡፡

የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ያለበትን ደረጃ ለማወቅ እንደመለኪያ በማገልገል ላይ ከሚገኙ መሣሪያዎች በአለም ዓቀፍ ደረጃ በብዙ ሀገሮች ተቀባይነት ያለው በየአራት ዓመት የሚከናወነው የሀገር አቀፍ የትምህርት ቅበላ ጥናትን (National Learning Assessment) ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይህንኑ ስልት በመጠቀም ለአብነት ያህል በ1999 ዓ.ም በተካሄደው በሦስተኛው የሀገር አቀፍ የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤት መሠረት በአራተኛና በስምንተኛ ክፍል የሚገኙ አብዛኛው ተማሪዎች የሁሉም ትምህርት ዓይነቶች ውጤት ከ50% በታች ሆኖ ተገኝቷል። በሌላም በኩል በየዓመቱ የሚሰጡ የሀገር አቀፍ ፈተናዎችና በአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ በተለያዩ ጊዜያት የሚካሄዱ የየደረጃውን የሥርዓተ ትምህርት አተገባበርን ለመገምገም የተዘጋጁ የፕሮፋይል ቴስቶችና ውጤቶች ከሀገር አቀፍ ትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ይህ የሚያሳየን ምንም እንኳ እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ በ2ኛውና በ3ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሀ ግብሮች የትምህርትን ጥራት ሊያስገኙ የሚችሉ ተግባራት ትኩረት ተሰጥቷቸው ጥረቶችና እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ናቸው። በመሆኑም ከላይ እንደተገለፀው በሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ለዘመናት ሰፍነው የቆዩትን የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ችግሮች በተቀናጀና በታቀደ መልኩ ለማስወገድ በሰኔ 1999 ዓ.ም የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ተቀርፆ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ስለሆነም በአፈጻጸም ሂደት የታዩ ዋና ዋና ችግሮችን በመለየት የሚመለከታቸው አካላት በተለይም የፖለቲካ አመራሩ የፓኬጁን ጽንሰ ሀሳብ በተገቢው ሁኔታ ጨብጠው ምልዓተ ህዝቡን በማንቀሳቀስ በሙሉ ባለቤትነት ስሜት ለመምራት ይችሉ ዘንድ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ የህዝብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ዕቅድ ሰነድ ተዘጋጅቷል። ክልሎችም በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ የተዘጋጀውን የህዝብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ዕቅድ እንደመነሻ በመጠቀም ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ በማድረግ የራሳቸው የህዝብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ዕቅድ አዘጋጅተው ወደ ስራ በመሰማራት እስከ ት/ቤት በየእርከኑ ዕቅዶች አዘጋጅተው፣ ሥልጠና እንዲሰጥ፣ግብአት እንዲሟላ፣ ድጋፍና ክትትል እንዲጠናከር በማድረግ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ተግባራዊ እንዲሆን ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል፡፡

ከዝህ በተጨማሪም የአጠቃላይ ትምህርት ስታንደርድ፣ የሳይንስና ሒሳብ ትምህርት እንዲሁም የሁለተኛ ትምህርት ስትራተጂዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት

ማረጋገጫ ፓኬጅ ስድስቱም ዋና ዋና ፕሮግራሞቹ የሚተገበሩት ለጥራት ግብዓቶችን፣ ሂደቶችንና ውጤቶችን ለማሻሻል ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም ከላይ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች የተገለፀው የመምህራን ቁጥር ዕድገት፣ ለደረጃው የሚመጥኑና የሰለጠኑ መምህራን ከዕቅድ በላይ መሆኑ፤ የአንደኛ ደረጀ ትምህርት (1-8) የተማሪ-መምህር ጥምርታ በ1997 ዓ.ም 54፡1 ከነበረበት በ2002 ዓ.ም 51፡1 ሲሆን በ2ኛ ደረጃ (9-12) ደግሞ በ1997 ዓ.ም 51፡1 የነበረው በ2002 ዓ.ም 36፡1 ሆኗል፡፡ የተማሪ- ክፍል ጥምርታን በተመለከተም በ1ኛ ደረጃ ትምህርት (1-8) በ1997 ዓ.ም 69 የነበረው በ2002 ዓ.ም 59፡1 ሲሆን በ2ኛ ደረጃ ትምህርት በ1997 ዓ.ም 78 የነበረው በ2002 ዓ.ም 68 ሊሆን ችሏል፡፡ የተማሪ-መጽሐፍት ጥምርታው በየክልሎች የተለያየ ገጽታ ቢኖረውም በሁሉም ደረጃ ጥምርታውን አንድ አንድ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል በአንደኛ ደረጃ ትምህርት መጠኔ ማቋረጥን ለመቀነስ ጥረቶች ብደረጉም ገና ይቀራል፡፡የ1ኛ ክፍል መጠነ ማቋረጥ በ1997 ዓ.ም 22.4% የነበረ ሲሆን በ2002 ዓ.ም 22.9% ሆኖ በመገኘቱ መጠኑ አልቀነሰም፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ የመድገም መጠንም እንዲሁ መሻሻልን አላሳየም፡፡

የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፓኬጅን አተገባበር በተመለከተ በእያንዳንዱ የፓኬጁ አበይት ጉዳዮች አፈጻጸም ዙሪያ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

ሥርዓተ-ትምህርትን በተመለከተ (የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጅን ጨምሮ) ችሎታንና ብቃትን መሰረት ያደረገ የሥርዓተ-ትምህርት ለውጥ ተደርጓል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ ከቅድመ መደበኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፎች፣ የሁሉም ትምህርት ዓይነቶች የአጥጋቢ ችሎታ መለኪያዎች፣ የፍሰት ሰንጠረዥ፣ መርሓ ትምህርቶች እና የተማሪና መምህር መጻሕፍት ተዘጋጅተዋል፡፡የሒሣብና የሣይንስ ትምህርቶች ስትራቴጅ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጅና መመሪያ ተዘጋጅተዋል፡፡

ሥርዓተ ትምህርቱን መሰረት አድርገው ከሚሰሩ መደበኛ የትምህርት ተግባራት አንዱ ምዘናና ፈተና ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በቂ የማቴሪያል፣ የገንዘብና የሰው ኃይል በመመደብ በ12ኛ ና 10ኛ ክፍል ደረጃ የሚሰጡ ብሔራዊ ፈተናዎችን በጊዜው በመስጠት፣ በማረምና የተማሪ ውጤትን በወቅቱ በማሳወቅ፣ ፍትሐዊ የሆነ የተማሪዎች የምደባ ሥርዓትን

በመከተልና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምረጫ መረጃን በመጠቀም የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፣ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን ደግሞ ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም ወደ 11ኛ (2ኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት) በመመደብ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በጊዜ እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፈተናዎች ምዝገባና የግል ተመዝጋቢዎችን ዶክመንት የማጣራት ሥራ ላይ አገዛ ተደርጓል፡፡ፈተና በማዘጋጀትና በማሳተም እራሳቸውን እንዲችሉ ለክልሎች የአቅም ግንባታ ስልጠናም ተሰጥቷል፡፡ የፈተና ውጤት መግለጫ መረጃ ለጠፋባቸው ተገልጋዮች የ12ኛ፣ የ10ኛ፣8ኛና 6ኛ ክፍል ድጋሚ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል፡ ፡ የትምህርት መረጃ ትክክለኛነት እንዲረጋገጥላቸው ለሚጠይቁ የግል አመልካቾች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የትምህርት ተቋማት፣ መስሪያ ቤቶች፣ ኤምባሲዎች፣ ወዘተ አግባብነት ያለው የማረጋገጥ አገልግሎት በየዓመቱ በተከታታይ ተሰጥቷል፡፡

የመምህራን ልማትን በተመለከተ በ3ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሐ ግብር ወቅት በርካታ አበረታች ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በመሆኑም የመምህራንን ሙያዊና አካዳሚያዊ ብቃት ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያለው የመምህራን ልማት መርሐ ግብር ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ሲሆን መርሐ ግብሩን ለመተግበርም የመምህራን ልማት ገዥ መመሪያ ተዘጋጅቶ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የአጠቃላይ ትምህርት መምህራን ብዛትም የቅድመ መደበኛ መምህራንን ሳይጨምር በ1997 ዓ.ም ከነበረው 188,720 በ2002 ዓ.ም 329,151 ደርሷል፡፡ ይህም በ1ኛና 2ኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ-መምህር ጥምርታውን እንዲሻሻል አድርጎታል፡፡ ከዚህ አንጻር በ1997 ዓ.ም 66 የነበረው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተማሪ-መምህር ጥምርታ በ2002 ዓ.ም ወደ 51 እንዲሁም በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ደግሞ 51 የነበረው ወደ 36 ተሻሽሏል። የመምህራንና የትምህርት አመራሮች የትምህርትና ሥልጠና መመሪያም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም የቅድመ-መደበኛ ትምህርት መምህራን በሰርቲፊኬት፣ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ዕርከን መምህራን በጥምር የትምህርት መስክ ሥልጠና ዲፕሎማ፣ የአንደኛ ደረጃ 2ኛ ዕርከን መምህራን በአብይ እና ንዑስ ትምህርት መስክ ሥልጠና ዲፕሎማ፣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን በሙሉ ደግሞ የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲኖራቸው እየተደረገ ሲሆን የትምህርት አመራሮችን ልማት በተመለከተም የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ዕርከን ትምህርት ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በዲፕሎማ፣ የአንደኛ ደረጃ 2ኛ ዕርከን ትምህርት ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በመጀመሪያ ዲግሪ፣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ደግሞ በማስሬት ዲግሪ የትምህርት ደረጃቸው

እንዲያድግ እየተደረገ ይገኛል።ይገኛል።በዚህም መሰረት በ2002 ዓ.ም የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ዕርከን በክረምት ስልጠና በክልሎች የሚሰጥ ከሴርተፊኬት ወደ ዲፕሎማ የወሰዱት ቁጥር ነባር 51-071 ሲሆኑ አዲስ 26,253 በድምር 77,374፤ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን በትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ ለነባሮቹ መምህራን 42,404፣ ለአዲሱቹ 12,462 በድምር ለ54,866 መምህራን ከዲፕሎማ ወደ ዲግሪ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና(up-grading) ወስደዋል፡፡

በቅድመ-አገልግሎት ለመምህርነት ሙያ ስልጠና የሚመለመሉ ዕጩ መምህራን የአመራረጥ መመሪያም ተዘጋጅቷል፡፡ ስለሆነም በችሎታቸው፣ ለመምህርነት ሙያ ባላቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲሁም ያላቸው መልካም ሥነ-ምግባር እየተረጋገጠ እንዲመለመሉና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዕጩ መምህራን በተግባራዊ ልምምድ የታገዘ ሥልጠና ተከታትለው እንዲያጠናቅቁ እየተደረገ ነው። የ2ኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ደግሞ በመረጡት የትምህርት መስክ እንደ አቻዎቻቸው ሁሉ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ችሎታቸው፣ ፈቃደኝነታቸውና ለሙያው ተገቢው ሥነ-ምግባር ያላቸውን በመመልመል በመምህርነት ሙያ እንዲሰለጥኑ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቷል። የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ- ትምህርትም አዲሱን/የተሻሻለውን/ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ ከ150,000 በላይ የአንደኛና 2ኛ ደረጃ ትምህርት መምህራንን ተጠቃሚ ያደረገ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በመምራን ማሰልጠኛ ተቋማትም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሻሻያ ማዕከላት ተቋቁመዋል፡፡ የመምህራን አሰልጣኞችን ብቃት ለማሳደግም የከፍተኛ ዲፕሎማ መርሐ ግብር ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን የመምህራንን አካዳሚያዊና ሙያዊ ብቃት እንዲሁም ሙያዊ ሥነ-ምግባር ለማሻሻል የሚረዳ የመምህራን የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ የሥራ ላይ ስልጠና በገገር መመሪያውና በተዘጋጀው የስልጠና ስትራቴጂ መሰረት በትምህርት ቤትና በጉድኝት ማዕከላት ደረጃ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ የመምህራንን የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና ዕድሳት አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋትም ቅድመ-ሁኔታዎች እየተመቻቹ ነው፡፡

የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ርዕሣነ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ብቃት ለማሳደግ የአመራርና ሥራ አመራር መርሐ ግብር ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን ይህን መርሐ ግብር በይበልጥ አጠናክሮ ለመቀጠልና እስካሁን ድረስ በትምህርት ዘርፍ በአገር አቀፍ ደረጃ በመንግስትና በልማት አጋሮች የተደረጉ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ያስገኙትን ውጤት፣ አሁን ያሉ

የአቅም ክፍተቶችና የስልጠና ፍላጎቶች እንዲሁም ለወደፊቱ መደረግ የሚገባውን የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራ የሚያሳይ የትምህርት ሥራ አመራርና አስተዳደር መርሐ ግብር ጥናትና ዲዛይን አዘጋጅቶ የሚያቀርብ ዓለም አቀፍ አጥኝ ቡድን ተቀጥሮ በመስራት ላይ ይገኛል። ይህ የሥራ አመራርና አስተዳደር መርሐ ግብር በትምህርት ዘርፍ ሥራ አመራርና አስተቃቀድ፣ በት/ቤት ዕቅድና ሥራ አመራር እንዲሁም በትምህርት ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራ ለመስራትና በሥራ አመራርና አስተዳደር ዙሪያ ዓይነታዊ ለውጥ በማምጣት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ታምኖበት የፓኬጁ አንድ ዋና አካል የሆነ መርሐ ግብር ነው፡፡

በመምህራንና የትምህርት አመራሮች ልማት ፕሮግራም ዙሪያ ከታዩ ተግዳሮቶች መካከል ቀጥሎ የተመለከቱት በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የት/ቤት አመራሮችና ተቋማት አሁንም ቢሆን የማስፈጸም አቅም ክፍተት ይታይባቸዋል፡፡ የመምህርነት ሙያ ተወዳጅነቱ እያደገ መምጣቱን ብንገነዘብም አሁንም ገና ከፍ ያለ አቅም ያላቸውን ዕጩዎች መሳብ ላይ ገና አልደረሰም። የሴቶች ተሣትፎም ገና ማደግ አለበት። የታዳጊ ክልሎች ብሔረሰቦች በመምህርነት ያለው ተሳትፎም ገና ማደግ አለበት። የዕጩ መምህራን ሥልጠና ጥራትና ለሥልጠናው የሚያስፈልግ ግብዓት በማሟላትና የተከታታይ ሙያዊ ስልጠናዎች አፈጻጸም ማጠናከርን ይጠይቃሉ።

የትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራምን በተመለከተ ከ1999 ዓ .ም ጀምሮ የትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ገዥ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ በየደረጃው ለሚገኙ አካላትም ስለ ፕሮግራሙ አተገባበር ሥልጠና ተሰጥቶ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ ት/ቤቶች ችግሮቻቸውን ለመለየትና የትምህርት ቤቶቻቸውን የማሻሻያ ፕሮግራም ለመንደፍ የሚያግዛቸው የትምህርት ቤቶች የግምገማ ቅፅ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በመሆኑም በአብዛኞቹ ክልሎች ያሉ 80% ያህል የአንደኛ ደረጃና 60% ያህል 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሦስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድና ዝርዝር ዓመታዊ ዕቅድ አዘጋጅተዋል፡፡የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፓኬጁን በብቃት ለመፈፀም እንዲቻል አንዱ ስልት በፓኬጁ አተገባበር ሂደት የተሻሉ አፈጻጸሞችና የተገኙ ውጤቶችን በመቀመር ለሌሎች ተቋማት በማስፋፋት መተግበር ነው፡፡ በዚህም መሠረት በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ ምርጥ ተሞክሮዎች ተቀምረው ለሁሉም ክልሎች ተሠራጭተዋል፡፡ ተጨማሪ ተሞክሮዎችን ከተመረጡ ትምህርት ቤቶች አሰባስቦ የመቀመርና የማሰራጨት ተግባር እየተከናወነ ሲሆን ቀሪው ጉዳይ እነዚህን የተቀመሩ ተሞክሮዎች ለሁሉም ክልሎች የማሠራጨት ሥራ ይሆናል፡፡

ከትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ርዕሰ ጉዳዮች አንዱ የሆነው ከወላጆች ጋር አብሮ መሥራት ሲሆን ለተማሪዎች ውጤት የራሱ ድርሻ ስላለው በዚሁ መሰረት ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ተገቢውን ተሣትፎ እንዲያደርጉ፣ ልጆቻቸውን እንዲያበረታቱና በትምህርት ቤቶች ላይ የባለቤትነት ስሜት ኖሯቸው እንዲሳተፉ የሚያስችል ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በሁሉም ክልሎች በመገኘት ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግም ለሞዴል የትምህርት ተቋማት፣  የርዕሳነ መምህራን፣ መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ የተማሪዎች፣ ወላጆችና ማህበረሰብ መለያ ተግባራት ባለድርሻ አካላትን ባካተተ መልክ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተሰራጭቶ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፓኬጅ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠሪያ አካል ሆኗል፡፡ በተጨማሪም የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራሙን በተጨባጭ ለመተግበር የሚረዳ የቅድመ መደበኛ፣ የአንደኛና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስታንደርድ ተዘጋጅቶ ከየክልሎች በተውጣጡ ባለሙያዎች ዳብሮ ክልሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉት ተሰራጭቷል፡፡

ትምህርት ቤቶችን መሰረት ያደረገ አመራርና አደረጃጀት ለማጎልበትና ህብረተሰቡንና የትምህርት ቤቶችን ሁሉም አካላት በማሳተፍ ውጤታማ፣ ዲሞክራሲያዊና ትምህርት ቤት ተኮር የሆነ አመራር ለማስፈን የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም በአንዳንድ ት/ቤቶች የተማሪዎች ዲሲፕሊንና ውጤት የመሻሻል አዝማሚያ አሳይቷል፡፡እንደዚሁም የተማሪዎች በወቅቱ ትምህርት ቤት ተገኝተው ትምህርታቸውን የመከታተል ሁኔታ ተሻሽሏል፡፡

ሥነ- ዜጋና ሥነ- ምግባርን በተመለከተ የየክፍል ደረጃው አጥጋቢ የችሎታ መለኪያ ተዘጋጅቶ በዚሁ መሠረት መርሀ ትምህርቶችን በማሻሻል፣ በተዘጋጁት አጥጋቢ የችሎታ መለኪያዎችና በተሻሻሉት መርሀ ትምህርቶች ላይ በመመሥረት ከ5ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ እያገለገሉ የሚገኙት የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍት ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲዘጋጁ ተደርገዋል፡፡ የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት በሥርዓተ ትምህርቱ ተካቶ መሠጠት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በትምህርቱ መማር ማስተማር ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን በተመለከተ ሁሉንም ክልሎች የዳሰሰ ጥናት ተደርጎ የጥናቱን ውጤት መሠረት በማድረግ ችግሩን ለማስወገድ ሥልጠና መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ለርእሳነ መምህራን፣ ለመምህራን፣ ለወላጅ መምህራን ህብረት፣ ለወረዳ ትምህርትና ሥልጠና ኃላፊዎች እና ለሱፐርቫይዘሮች ሥልጠና ተሰጥቷል፡ ለሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት አተገባበር በመመሪያነት የሚያገለግል ገዥ ሰነድ ተዘጋጅቶ፣ በባለሙያዎችና በባለድርሻ አካላት ተተችቶ ሰነዱ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት እሴቶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ እየተሰጡ በሚገኙ የታሪክና የጂኦግራፊ ትምህርቶች ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት መምህራንን አቅም ለመገንባትና በትምህርቱ ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለማስተካከል እንዲያስችል ለመምህራን፣ ለሱፐርቫይዘሮችና ለሌሎችም ባለድርሻ አካላት በፕላዝማ ቴሌቪዥን የተደገፈ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየተሰጠ ለሚገኘው የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ለዲግሪ፣ ለዲፕሎማና ለጋራ ትምህርት የሚያገለግሉ ሥርዓተ ትምህርቶች ከሁሉም ዩኒቨርስቲዎችና የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ከተውጣጡ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርትን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለማስረጽ የሚያስችል መመሪያም ተዘጋጅቷል፡፡

## 2.3. <u>ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና</u>

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በመካከለኛ ደረጃ የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ቁልፍ ሚና የሚጫወት ዘርፍ ነው። ከዚህ አንጻር በ3ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ትግበራ ወቅት በዚህ ዘርፍ በተሟትፎና በማስፋፋት ዙሪያ በርካታ ተግባራት ተከናወነዋል።በመሆኑም በ1997 ዓ.ም 106,336 የነበረው የቴ/ሙ/ትምህርትና ሥልጠና ተሟትፎ በ2002 ዓ.ም ወደ 615,913 ያደገ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ50% በላይ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትም ወደ 253 ደርሰዋል።

በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ተመርኩዞ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን በቴክኖሎጂ አቅማቸውን ከማሳደግ አንፃር በአገር አቀፍ ደረጃ ትኩረት በተሰጣቸው 7 ኢንዱስትሪዎች /ጨርቃጨርቅ፣ ቆዳ፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ግብርና፣ ኮንስትራክሽን፣ ሜታል ማኑፋክቸሪንግና ሆቴል ቱሪዝምና ቢዝነስ/ የአመራረትና የአሰራር እሴት ሰንሰለት ትንተና በማካሄድ 200 የሚደርሱ የቴክኖሎጂ ክፍተቶች የተለዩ ሲሆን 137ቱ ቴክኖሎጂዎች ከተለያዩ አማራጮች ተገኝተዋል፡፡ ቴክኖሎጂ ለመምረጥ በተቀመጡት መስፈርቶች ማለትም ምርታማነት፣ የምርት ጥራት፣ ጉልበት በስፋት መጠቀምና የዋጋ አዋጭነት በመጠቀም 126 ቴክኖሎጂዎች ተመርጠው የ99ኙ ንድፍና ናሙና ተዘጋጅቶ የፍተሻ ሥራ ተከናውኗል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 44ቱ ቴክኖሎጂዎች ተባዝተው ለተለያዩ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት

የተሰራጩ ሲሆን ተጨማሪ 29 የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎች ለማሰራጨት ተጠቃሚዎችን የማብቃት ስራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አጠቃላይ ሀገር አቀፍ የቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ሥራ ውጤቶችን ሥርዓት ባለው መልክ ለማደራጀትና መረጃውን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ለማድረስ የሚያስችል የመረጃ ቋት ከክልሎች ጋር በመሆን ተዘጋጅቷል፡፡ የቴክኖሎጂ አቅም የማከማቸትና የማሸጋገር ዝርዝር የስራ ፍሰትን የያዙ የአሰራር ሥርዓት ሰነዶችን ተመርኩዞ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን ስራ የሚያግዙ የማስፈፀሚያ ማንዋሎች ማዘጋጀትን በተመለከተ የእሴት ሰንሰለት ማፕ የማዘጋጀትና ችግሮችን ተንትኖ በቅድም ተከተል ለማስቀመጥ የሚረዳ ማንዋል ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ በቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ሥራ የተገኙ ልምዶችንና ጥሩ ተሞክሮዎችን በመመርኮዝ ሁሉንም ስራዎች ያካተተ አንድ ወጥ ማኑዋል ለማዘጋጀት ከክልሎች ከተውጣጡ የቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር የሥራ ሂደት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በተደረሰ ስምምነት መሰረት ማንዋሉ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም በክልሎች እየተከናወነ ያለውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደት ለመደገፍ ከ8 ክልሎች ለተውጣጡ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራ ሂደት ቡድን አባላት ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን እንዴት ማፈላለግ፣ መለየት፣ ማቀብና ማሸጋገር እንደሚቻል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ቴክኖሎጂዎችን ከማከማቸት አኳያ በርካታ ቴክኖሎጂዎች ተባዝተው ለትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብና አዲስ አበባ የተሰራጩ ሲሆን በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራው ላይ እየተጠቀሙበት መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የመምህራንን የማሰልጠን ብቃት ለማጎልበት የመምህራንን የክህሎት ክፍተት ከሙያ ደረጃዎች አንጻር በመለየት የማብቃት ሥራ ተጀምሯል፡፡ የክህሎት ብቃታቸውም በምዘና ተረጋግጧል፡፡ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መምህራን የማብቃት ማዕቀፍ ተጠናቆ በ A ደረጃ ለሚገኙ መምህራን ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት የሚረዳ የሞጅዩል ዝርዝር የተዘጋጀ ሲሆን ነባር የ B ደረጃ መምህራንን ከማብቃት አንጻርም በአገሪቱ ውስጥ በመንግስት ተቋማት ውስጥ በ B እና C ደረጃ ካሉ ነባር መምህራን ውስጥ ምዘናውን ወስደው ላለፉ መምህራን ተግባር ተኮር የማስተማር ሥነ ዘዴ ሥለጠና ተሰጥቷል፡፡

በየጊዜው የሚኖረውን የሥራ ገበያ ፍላጎት መረጃ ለመለየትና ለማወቅ የሚያስችል መነሻ ሰነድ እና የሰልጣኞች የሙያ ምክርና ድጋፍ እንዲሁም ተቋምን ከኢንዱስትሪው ጋር ለማስተሳሰር የሚረዳ የሙያ ምክር ድጋፍ አገልግሎት መመሪያ ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚሰጠው

ስልጠናም የሙያ ደረጃንና የገበያ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሠልጣኞች በሥራው ዓለም ውስጥ ያላቸው ተፈላጊነት በከፍተኛ ሁኔታ ተሻሽሏል፡፡ በአዲሱ የመካከለኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ሰልጣኞች ከኢንዱስትሪ ጋር የሚተዋወቁበት ስልት በተለይ በመደበኛው ፕሮግራም ውስጥ ተካቷል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማሳደግና ምሩቃኑም የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ በተቋማቱና በአሰሪ ድርጅቶች ጠንካራና በመተጋገዝ ላይ የተመሰረተ የትብብር ሥልጠና እና የሥራ ላይ ልምምድ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

የተቋማትን አሰራር ለማሻሻልና ለጥራት ማረጋገጫ የዓለም አቀፍ ደረጃዎች ድርጅት/ISO 9001 ሥርዓት ብቁ ለማድረግ 10 የሙከራ ተቋማት ተመርጠዋል፡፡ በዚህ መሰረት ከአዲስ አበባ 5 እና ከክልሎች 5 ተቋማት የተመረጡ ሲሆን የመጀመሪያ ዙር ከአዲስ አበባ የእንጦጦ፣ ተግባረ ዕድ ፣ ዊንጌት፣ ሠላምና ኤስ ኦ ኤስ (SOS) ኮሌጆች የሦስተኛ አካል የዶክዩመንቴሽንና አደረጃጀት ኦዲት አልፈው ለመጨረሻ ኦዲት ዝግጁ ሆነዋል፡፡ እስካሁን በተከናወነው ሥራ በተለይ የወርክ ሾፕ አደረጃጀትና አሰራርን ቀልጣፋ በማድረግ ጥሩ ውጤት የታየ ሲሆን በቀጣይነት በጉድኝት ደረጃ ወደ ተደራጁ ተቋማት የማስፋት ሥራ ይከናወናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአብዛኞቹ ክልሎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በኤጀንሲ ደረጃ ራሱን ችሎ የሚሰራበት አደረጃጀት ተዋቀሯል፡፡ የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትም በቦርድ የሚመሩበት አደረጃጀት ተፈጥሯል፡፡ የትብብር ስልጠና ስርዓት ማሻሻልን በተመለከተም ቀደም ሲል ሲሰራበት የነበረውን የትብብር ስልጠና ስርዓት ማንዋል አዳዲስ ልምዶችና ተሞክሮዎችን በማካተት ለተጠቃሚው የተሻለ መረጃ መስጠት በሚችል መልኩ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ የትብብር ስልጠና ማስፋፋትን በተመለከተም በሁሉም የሙያ ዓይነቶች የሚሰጡ ስልጠናዎች በሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ ተሳታፊነት በትብብር ስልጠና ዘዴ እንዲሆን ከክልሎች ጋር ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን ለዚህ የሚያግዝ መመሪያም ለክልል አስፈጻሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡በዚህ መሰረት በአሁኑ ወቅት 163,509 ሰልጣኞች በመላው አገሪቱ የትብብር ሥልጠና እየተከታተሉ ሲሆን የኩባንያ ውስጥ ስልጠናን ከሙያ ደረጃ፣ ምዘናና ቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር በማስተሳሰር ኢንዱስትሪውን በብቁ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ ለመመገብ የሚያስችል ፍሬም ወርክ ተቀርጿል፡፡ የኩባንያ ውስጥ ሥልጠናን በፍጥነት በኩባንያዎች ውስጥ ለማስረፅ በላቀ ደረጃ በመተግበር ላይ ያሉ ኩባንያዎችን ሌሎች ኩባንያዎች እንዲጎበኙ በማድረግና ደከም ያለ

አፈጻጸም ላሳዩ ኩባንያዎች የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ በማገዝ የኩባንያ ሥርዓቱ በፍጥነት እንዲዘረጋ ማድረግ ተችሏል፡፡ የኩባንያ ውስጥ ሥልጠና በተጀመረባቸው ኩባንያዎችም አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገቡ መሆኑም ታውቋል፡፡

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ደረጃ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ከመነሻቸው የየኢንዱስትሪ ዘርፉን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ያማከሉ መሆን እንዳለባቸው ካለው አጠቃላይ ግንዛቤ በመነሳት በ18 ዘርፎች 249 በሥራ ገበያ ላይ ተፈላጊ የሆኑ ሙያዎች የተለዩ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 232ቱ የሙያ ደረጃ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በተለይም በኮንስትራክሽን፣ በኤሌክትሪሲቲና ኤሌክትሮኒክስ፣ በሜታል ማኑፋክቸሪንግ፣ በአውቶሞቲቭ፣ በቴክስታይልና ጋርሜንት፣ በውሃ ሥራዎች፣ በግብርናና ሆቴልና ቱሪዝም ዘርፎች ለተለዩ ሙያዎች በሙሉ በተለያዩ የሙያ ደረጃዎች ሊቀጠሩና በራሳቸው በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው ሥራ የሚፈጥሩ በርካታ ሙያተኞችን ማፍራት እንዲቻል ለየሙያዎቹ ከዝቅተኛው ጀምሮ ደረጃዎች ተለይተው የሙያ ደረጃ ሰነዶች ተዘጋጅተውላቸዋል፡፡

ቀደም ሲል የነበሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን ተከታትለውም ይሁን በተላያዩ መንገዶች ሰልጥነውና በየመስኩ ተሰማርተው የሚገኙትን እንደዚሁም በቀጣይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓታችን በሚያበረታታቸው የተለያዩ አካሄዶች ሰልጥነው ወይም ራሳቸውን አብቅተው በዕጩነት የሚቀርቡ ዜጎችን ከሙያ ደረጃዎችና ከኢንዱስትሪው ፍላጎት አኳያ መመዘን እንዲቻል ከሁሉም ዘርፎች ቅድሚያ ለተሰጣቸው 84 ሙያዎች የምዘና መሳሪያዎች ተዘጋጅተው በአገሪቱ በሚገኙ 6 የልህቀት ማዕከላት በሙያዎቹ ላይ የብቃት ምዘና መስጠት ተጀምሯል፡፡ የብቃት ምዘና መስጠት ከተጀመረ ወዲህ በ6ቱም የልህቀት ማዕከላት በኩል ለ39,510 ዕጩዎች የብቃት ምዘና ተሰጥቶ 9,643 (24.41%) ዕጩዎች ብቁ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

ሆኖም ግን በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አተገባበር ወቅት የተከሰቱ ችግሮች ነበሩ፡፡

ከእነሱም በዋኛነት የሚጠቀሱት ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው፡፡

- በሕብረተሰቡ፣ በባለድርሻ አካላት፣ ባስፈፃሚና በፈፃሚ አካላት እና በሰልጣኞች ዘንድ ስለውጤት ተኮር ቴ/ሙ/ት/ስ/ ስርዓት ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆንና ሰልጣኞች የቴ/ሙ/ት/ስ ፕሮግራምን ወደ ከፍተኛ ትምህርት መሸጋገሪያ አድርገው ማሰባቸው፡፡
- የቴ/ሙ/ት/ሥ/ ተቋማት ቴክኖሎጂን ለማሸጋገርና ለማስረጽ ብቁ ሆነው አለመገኘት፣

- ህጋዊ መሠረት ያለውና ባለድርሻ አካላትን ያሣተፈ አደረጃጀት አለመኖር፣
- የሥራ ፍላጎት ጥናት ሥርዓት አለመኖር፣
- በየደረጃው ያሉ ባለሙያዎች ብቃት ስርዓቱን በአግባቡ ለመተግበር ያለማስቻሉ፣
- ተከታታይ የሆነ ክትትልና ግምገማ የማካሄድ ብቃት አለመኖር፣
- የተሟሉ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ስትራቴጂ ማስፈፀሚያ ሰነዶች አለመኖር፣
- የተሟላ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና ልውውጥ ስርዓት አለመኖር፣

## 2.4. <u>ከፍተኛ ትምህርት</u>

ከፍተኛ ትምህርት በ1997 ዓ.ም ከነበረበት ሁኔታ አበረታች ዕድገት አሳይቷል፡፡ በመንግስት ተቋማት ብቻ በ1997 ዓ.ም ከነበረው 78,232 ጠቅላላ የመጀመሪያ ዲግሪ መደበኛ ተማሪ ብዛት በ2002 ወደ 185,788 (በ137.5 መቶኛ) አድጓል፡፡ በ1997 ዓ.ም 24% የነበረው የሴት ተማሪዎች ድርሻ በ2002 ዓ.ም 29% ሆኗል፡፡ የድሕረ ምረቃ ትምህርት ተሳትፎም በ1997 ከነበረው 3,604 ተማሪዎች በ2001 ወደ 9,761 አድጓል፡፡ የሴት ተማሪዎች ድርሻ ከ9% ወደ 11.3% አድጓል፡፡ በዚያው ዘመን የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ብዛት በ13 ጨምሮ 22 ደርሷል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ዓመታዊ የቅበላ መጠን በ2001 ዓ.ም 79,500 ተማሪዎች ነበር፡፡ ይህ መጠን ዓመታዊ ቅበላ ሲሆን በ2002 ወደ 77,182 ዝቅ ብሏል፡፡ በ2002 ዓ.ም ለቅበላ መጠን ከ2001 ዓ.ም ዝቅ ማለት ምክንያቱ የህንጻ ግንባታዎች በታሰበው አለመፋጠን ነው፡፡ በመርሃ ግብሩ ዘመን የከፍተኛ ትምህርት ስርዓቱን ወደ ዓይነታዊ ለውጥ ሊያደርሱ የሚችሉ በርካታ መሰረታዊ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ተልዕኮአቸውን ለማሳካት የሚያስችላቸውን የማስፈጸም ዓቅም ለመገንባት በተቋማዊ ለውጥ ሂደት ውስጥ ገብተዋል፡፡ ይህን ሂደት የሚያጠናክርና የውጤቱን ዘላቂነት የሚያስጠብቅ ሕጋዊ ማዕቀፍም ተዘርግቷል፡፡

በመንግስት ዩኒቨርስቲዎች የቅድመ ምረቃ ትምህርት ተሳትፎ ዕድገት በሳይንስና ቴክኖሎጂ መሪነት (በ70:30) እንዲቃኝ አቅጣጫ ተቀምጦ በ2002 ዓ.ም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ድርሻ ከጠቅላላው 185,788 ተማሪዎች 55.7% ሲሆን ከዓመታዊ ቅበላው (77,182) ደግሞ 58% ላይ ደርሷል፡፡ በ2002 በኢንጅኔሪንግና ኮምፒዩቲንግ በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች 31,373 ነው። መረጋገጥ የሚገባው የተሳትፎ ዕድገት እንደተጠበቀ ሆኖ የኤንጅኔሪንግና የኮምፕዩቲንግ መስኮች ምድብ የተቀመጠለት የ40% ግብ ላይ ለመድረስ በነባር ዩኒቨርስቲዎች የማስፋፋት ግንባታን ማከናወንና በትምህርት መሣሪያዎች

የማደረጀት እንዲሁም አዲስ ዩኒቨርስቲዎችን መገንባትና ማደራጀት ይጠይቃል፡፡ የተጠቀሰውን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል የአመራርና የአስተዳደር ስርዓት የመገንባትና የቅድመ ምረቃ ትምህርትን አግባብነት በኢንዱስትሪ ልማት የሰው ኃይል ፍላጎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲመራ የማድረግ መልካም እርምጃዎች ጋር በማስተሳሰር የትምህርት ጥራቱን ለማረጋገጥ በሚያስችሉ የስርዓተ ትምህርትና የመምህራን ልማት ቁልፍ ጎዳዮች ላይ የተቀመጡ አቅጣጫዎችና የተከናወኑ ስራዎች አሉ፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገትን በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለማሳለጥ የኤንጂኔሪንግ እና የተፈጥሮ ሳይንስ ስርዓተ ትምህርቶች ለውጥ ተጠናቆ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ አዳማ ዩኒቨርስቲን የቴክኒካል ዩኒቨርስቲ ሆኖ እንዲገነባና የዘጠኝ ዩኒቨርስቲዎች የቴክኖሎጂ ፋክልቲዎችን የአስተዳደር ነጻነት ባላቸው የቴክኖሎጂ ኢንስቲቱዩቶች እንዲደራጁ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

የአገሪቱ ልማትና ዕድገት አስተማማኝ የፍትህ ስርዓትን መገንባት ስለሚጠይቅ የሕግ ስርዓተ ትምህርቱ በዚሁ ቅኝት ተለውጦ መተግበር ተጀምሯል፡፡ የቢዝነስና ኤኮኖሚክስ፣ የህክምናና ጤና ሳይንስ፣ የግብርናና የማሕበራዊ ሳይንስ ስርዓተ ትምህርቶችም ተለውጠው ወደ ትግበራ ተሸጋግረዋል፡፡ የህክምና አዲስ ስርዓተ ትምህርት ቀረጻም የማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ነው፡፡

የተለወጡት ስርዓተ ትምህርቶች ትግባራ ብቁ መምህራንን ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ ረገድም የመምህራን ልማት ስትራቴጂን በመቅረጽ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም በ1997 ዓ.ም 4,847 የነበረው የዩኒቨርስቲ መምህራን ብዛት በ2002 ዓ.ም ወደ 11,238 አድጓል፡፡ ከነዚህ መምህራን መካከል ገና የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 5,706 (50.8%)፣ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ 4,528 (40.3%) እና ፒኤች ዲና አቻ ዲግሪ ያላቸው 1,004 (8.9%) ናቸው፡፡ የድሕረ ምረቃ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙት 5,826 (4,681 የ2ኛ ዲግሪ እና1,145 የፒ ኤች ዲ ዲግሪ) ሲታከልበት የዩኒቨርሲቲ መምህራን ብዛት 17,064 ይሆናል፡ ፡ ይህ ገና በመጀመሪያ ዲግሪ ክልል ያሉትን መምህራን ምጣኔን ወደ 33.4% ዝቅ ያደርገዋል፡፡ ይሁንና በማስተማር ስራ ላይ ያሉትን ብቻ ግምት ውስጥ በማስገባት በ2002 ዓ.ም የተማሪ/መምህር ጥምርታ ባጠቃላይ 1፡16 ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ ካላቸው መምህራን አንጻር ግን 1፡34 ነው፡፡

የትምህርት አግባብነትና ጥራት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችንም ይጠይቃሉ፡፡ ነባር ዩኒቨርስቲዎች የካፒታል በጀትን ለማስተዳደር በተሰጣቸው ውክልና መሠረት በጀታቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ ሲሆን ለአዲሶቹ ዩኒቨርስቲዎች ግን ከማዕከል ይቀርብላቸዋል፡፡ ይሁንና በነባሮቹም ይሁን በአዲሶቹ አቅርቦቱ ፍላጎትን ያለማርካትና ያለውን አቅርቦት ደግሞ በሚገባ ያለመጠቀም ክፍተቶች ገና ያልተወገዱ ችግሮች ናቸው፡፡

የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ለማሳካት የተደራጀ ሙያዊ ሃገራዊ አመራርን ለማረጋገጥ ሲባል የስትራቴጂ ማዕከልና የትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ተቋቁመዋል፡፡ እነዚህ አካላት በዋናነት ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸውን የማስፈጸም ዓቅም በመገንባት ሂደት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ባጠቃላይ የመንግስቱ ዘርፍ የከፍተኛ ትምህርት የትምህርት አግባብነትና ጥራትን ባማከለ የለውጥና ዕድገት አቅጣጫ ላይ ይገኛል፡፡ ይሁንና አሁንም ዓይነታዊ ለውጥን ለማረጋገጥ በሚያስችለው የለውጥ ሂደት ውስጥ እንጂ ማረጋገጥ ካለበት ዓይነታዊ ለውጥ ላይ ገና አልደረሰም፡፡ የግሉን ዘርፍ በተመሳሳይ አቅጣጫ እንዲመራ የማብቃቱ ተግባር ባጠቃላይ ገና መሰራት ያለበት ትልቅ ጉዳይ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

በአብዛኞቹ ዩኒቨርሲቲዎች የሥርዓተ ጾታ ጽ/ቤት ተቋቁሞ ለሴት ተማሪዎች የተለያዩ የድጋፍ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በተለይም ሴት ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግና ትምህርታቸውን አቋርጠው እንዳይወጡ በዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ የማብቃት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በዩኒቨርሲቲዎች በመከናወን ላይ ከሚገኙ የማብቃት ሥራዎች መካከል ነባር ሴት ተማሪዎች አዲስ ለሚገቡ ሴት ተማሪዎች ልምዳቸውን የሚያካፍሉበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሴት ተማሪዎች ማህበር ተቋቁመዋል፡፡ ከየክፍሉ የተመረጡ ምርጥ አምስት ሴት ተማሪዎች ለክፍል ጓደኞቻቸው ደጋፊ ትምህርት መስጠት ጀምረዋል፣ ውጤታማ ለሆኑ ሴት ተማሪዎች ሽልማት የመሰጠትና ማበረታታት ሥርዓት ተጀምሯል፡፡ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን ሴት ምሁራንና ኃላፊዎች በመጋበዝ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሴትነታቸው የሚያጋጥሟቸውን አሉታዊ ተፅእኖዎች ተቋቁመው ውጤታማ እንዲሆኑ በተከታታይ የኦረንቴሽን ፕሮግራም ተካሂዷል፣ ዩኒቨርሲቲዎች ሴት ተማሪዎችን በትምህርታቸው እኩል ተወዳዳሪ ለማድረግ የጀመሩዋቸው መልካም ጅምሮችን አጠናክረው እንደሚቀጥሉባቸው እናምናለን። በሴት ተማሪዎች የሚደርሱ ማንኛውም ዓይነት ተፅዕኖ፣ ትንኮሳና ጥቃትን ለማስወገድ በመዘርጋት ላይ ያሉትን ሥርዓትም አጠናክረው ይቀጥሉበታል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊ ለውጥን በተመለከተም ዩኒቨርስቲዎችን በቦርዶች የማደራጀትና በተለይ ለውጡን በመምራት ላይ ከኃላፊነታቸው ጋር የማስተዋወቅ ስራ

ተሰርቷል፡፡ ዝርዝር የመከታተያ ነጥቦችም እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ የዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቶች ሹመት በቦርዶች ተደግፎ እየቀረበ በወሳኝነት ተፈጽሟል፡፡ የምክትል ፕሬዚዳንቶች ሹመትም በቦርዶች በወሳኝነት ተፈጽሟል፡፡ የአስተዳደር ካውንስሎች ተደራጅተው ስራ ጀምረዋል፡፡ሰኔቱን ዳግም የማደራጀቱ ጉዳይ የማቋቋሚያ ደንቦችን መጽደቅ ስለሚጠይቅ ገና ነው፡፡ በነባር ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የቴክኖሎጂ ኢኒስቲቱዩቶችን የማደራጀቱ ስራ በመከናወን ላይ ነው፡፡ እስካሁን ለአምስት ኢኒስቲቱዩቶች የሚመጥኑ የውጭ ምሁራን ለመመልመልና ለመመደብ ተችሏል፡፡ የራሳቸው ቦርዶች የማደራጀቱም ሥራ ተፈጽሟል፡፡ የዩኒቨርስቲዎች ማቋቋሚያ ደንቦችን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ለማቅረብ በሚቻልበት ደረጃ በሁለት ናሙናዎች መልክ ተዘጋጅተዋል፡፡ ዓዋጁን በሚመለከት ደግሞ ለዩኒቨርስቲ ቦርዶችና ከፍተኛ መሪዎች በተለያዩ የጥልቀት ደረጃዎች ማስተዋወቅ ተደርጓል፡፡

በዚህ አጠቃላይ ዕይታ ክልል የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የሚከተሉት ድክመቶች ያሉበት መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

- የከፍተኛ ትምህርት አመራርና አስተዳደር ስርዓቱ በሚፈለገው የብቃት ደረጃ አልደረሰም።
- የመምህራን ልማትን ሁሉም ገጽታዎች አስተሳስሮ መፈጸም ገና ስርዓት አልሆነም፡፡
- ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት መምህራን የትምህርት ደረጃ ቢያንስ 2ኛ ዲግሪ የሆነበት ደረጃ ገና አልደረሰም።
- የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥርዓት አለመኖር፣በተለይ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች የኢንዱስትሪ ልማት የሰው ኃይልና የቴክኖሎጂ ሽግግር ፍላጎትን ለመመለስ የሚያስችል የማስፈጸም ዓቅም ግንባታው ገና ሂደት ላይ ያለ ነው፡፡ መረጋገጥ የሚገባው የተሳትፎ ደረጃም ገና አልተደረሰበትም፡፡
- በ70፡30 የመስኮች ምጣኔ ክልል የቴክኖሎጂ ድርሻ ከሆነው 40% ግብ ላይ ገና አልደረሰም።
- የቅድመ ምረቃና ድሕረ ምረቃ የቅበላ ዓቅሞች ገና በግንባታ ሂደት ላይ ናቸው፡፡
- የሴት ተማሪዎች ድርሻ በቅድመ ምረቃውና በድሕረ ምረቃው ፕሮግራም ገና አነስተኛ ነው።

- የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ገቢን የማመንጨትና የማሳደግ ዓቅም ገና ውሱን ነው፡፡
- የግሉ ዘርፍ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ገና ፈር እንዲይዝ አልተደረገም፡፡

## 2.5. የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች

ባለፉት አምስት ዓመታት በሁሉም የትምህርት ዘርፍ እንቅስቃሴዎች ተካተው ሲሰራባቸው የነበሩ የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ሥርዓተፆታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ ልዩ ፍላጐትና አካቶ ትምህርት፣ የህብረተሰብ ተሳትፎና ያልተማከለ የትምህርት ሥርዓትና የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ናቸው ፡፡

ሥርዓተ -ፆታን በተመለከተ በወንድና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለውን የትምህርት ተሣትፎ ልዩነት ለማጥበብ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ብሔራዊ የልጃገረዶች ትምህርት ስትራቴጅና ሥርዓተ-ፆታን በሁሉም ተግባራት የማካተት መመሪያ ተዘጋጅተዋል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ በርካታ የሥርዓተ-ፆታ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችና ሥልጠናዎች ተካሂደዋል፡፡ በየትምህርት ተቋማቱ የሥርዓተ -ፆታ ማዕከላትና ክበባት ተቋቁመዋል፡፡ ሥርዓተ-ትምህርቱና የሥልጠና ሂደቱ ሥርዓተ- ፆታን ያካተተ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የተለያዩ የሥርዓተ-ፆታ ጥሰቶችን ለመከታተልና ለመከላከል ከየሴክተር መስሪያ ቤቶች ከተቋቋመው የጋራ ኮሚቴ ጋር በመሆን በሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች ላይ የመከታተልና የመከላከል ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚገቡ ሴት ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ በመሰጠቱ በከፍተኛ ተቋማት የሴቶች ተሣትፎ እያደገ መጥቷል፡፡ በመሆኑም በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በሴቶችና በወንዶች መካከል የነበረው የጥቅል ተሣትፎ ልዩነት እየጠበበ መጥቷል። በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሣትፎ ዙሪያ የሥርዓተ- ፆታ ልዩነት ምጣኔው በ1997 ከነበረበት የወንዶች 0.87 እና የሴቶች 0.69 በ2001 ዓ.ም ወደ 0.93 እና 0.92 መጥቷል፡፡ ይሁን እንጅ በተለይ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስለጠና እና በከፍተኛ ትምህርት፣ በማስተማርና በትምህርት አመራር ደረጃ የሴቶች ተሣትፎ አነስተኛ በመሆኑ በዚህ ረገድ ልዩነቱን ለማጥበብ ከፍተኛ ሥራ መስራት ይጠይቃል፡፡

ኤች አይ ቪ ኤድስን መከላከልን በተመለከተ በሦስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ ባሉት ሥርዓተ ትምህርቶች ኤች አይ ቪ ኤድስን በማካተት ሰለ ኤች አይቪ ምንነት፣ስለመተላለፊያው ሁኔታና እንዴት መከላከል እንደሚቻል

ለህጻናትና ወጣቶች ትምህርትና ግንዛቤ በመሰጠት ላይ ነው፡፡ በቅርቡ በተለወጠውና ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በሚተገበረው ሥርዓተ ትምህርት ደግሞ ኤች አይ ቪ ኤድስ ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ ባሉት ሥርዓተ ትምህርቶች ውስጥ ተካቷል፡፡ እንደዚሁም ጉዳዩ በመምህራን ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት የተካተተ ሲሆን ጉዳዩን የሚከታተሉ ተጠሪዎች በፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር፣ በክልልና ወረዳ ደረጃ ተመድበው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በሁሉም የትምህርት ተቋማትና የትምህርት ዕርከኖች ደረጃ የፀረ-ኤች አይቪ /ኤድስ ክበባት ተዋቀረዋል፡፡ የትምህርት ዘርፍ በኤች አይቪ /ኤድስ መከላከል ላይ የሚያካሂደውን ሥራ ይበልጥ ውጤታማ ለማድርግም የትምህርት ዘርፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፖሊሲና ስትራቴጅ ተዘጋጅቶ ፀድቋል፡፡

በሦስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስን ታሳቢ በማድረግ ለልዩ ፍላጐትና አካቶ ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጅ ተዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ነው፡፡ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የመተዋወቂያ ኮርስ በሁሉም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ በአራት ዩኒቨርሲቲዎች በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ፣በአምስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በዲፕሎማ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማስትሬት ዲግሪ ደረጃ የልዩ ትምህርትና አካቶ ትምህርት ፕሮግራም በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሥነ ልሣን የትምህርት ክፍል የምልክት ቋንቋ በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ በዘጠኝ ክልሎችና ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ለትምህርት ቢሮ የትምህርት ባለሙያዎችና ለሁሉም የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊዎች በልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡

ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎችም ተጨማሪ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተፈጠረው ግንዛቤ የተነሣ ከ1999 በፊት ከ33,000 በታች የነበረው የአካል ጉዳተኛ ህጻናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሣትፎ በ2001 ዓ ም በተገኘው መረጃ መሰረት ወደ 41,300 ደርሷል፡፡ የልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት በዋና ዋና የትምህርት ዓይነቶች ሥርዓተ ትምህርት የተካተተ ሲሆን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው ለመርዳት የሚያስችሉ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተመረጡ ሦስት ልዩና ስድስት ክላስተር ትምህርት ቤቶች በድጋፍ መስጫ ማዕከልነት ተዋቅረዋል፡፡ ለልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት ተንቀሳቃሽ መምህራን ተቀጥረው በመሥራት ላይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የዋና ዋና ትምህርቶች ሥርዓተ ትምህርት የአካል ጉዳተኛ ሕጻናት ትምህርትን እንዲያካትት የተደረገ ሲሆን ለአካል

ጉዳተኛ ህጻናት የተለየ ሥርዓተ ትምህርት ለማዘጋጀት የሚያስችል መመሪያም እየተዘጋጀ ነው።

ከህብረተሰብ ተሳትፎ አኳያ ያለፈው የትምህርት ዘርፍ መርሐ ግብር ትግበራ ከፍተኛ የማህበረሰብ ንቅናቄና ተሣትፎ የታየበት ነበር፡፡ በመሆኑም በርካታ የአንደኛና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማህበረሰብ ተሣትፎ በመሰራታቸው የተማሪ ጥቅልና ንጥር ተሳትፎ ጨምሯል፡፡ ይህንም ከላይ ከቀረበው ሪፖርት መመልከት ይቻላል፡፡ የማህበረሰቡ ተሣትፎ ጉልበቱን፣ ገንዘቡን፣ ማቴሪያልና ዕውቀቱን በመለገስ ብቻ ሳይሆን ልጆቹን በእድሜያቸው ወደ ት/ቤት በመላክና በመርዳት ጭምር የተንጸባረቀ እንደነበር የተለያዩ ዓመታዊ ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡ ለምሣሌ በኦሮሚያ ክልል ሁሉም የመጀመሪያ ደረጃና ሦስት-አራተኛ ያህሉ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተገነቡት ፣የታደሱትና የተስፋፉት በማህበረሰብ ተሣትፎ እንደነበር ተውቋል፡፡ በአማራ ክልልም በማህበረሰቡና በክልሉ መንግስት መካካል የትምህርት ቤት ግንባታ ወጭ መጋራት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በሌሎችም ክልሎች በተመሣሣይ ሁኔታ የማህበረሰብ ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ በመቀጠሉና ት/ቤቶች ወደ ሕጻናት መኖሪያ አካባቢዎች በመቅረባቸው ሕጻናት ወደ ት/ቤት ለመሄድ የሚፈጅባቸው ጊዜና ድካም በተወሰነ ደረጃ ቀንሷል፡፡ ይህም በተለይ የሴት ሕጻናትን የትምህርት ተሣትፎ አሳድጓል፡፡

ይሁን እንጅ ማህበረሰቡ በትምህርት ላይ ሊኖረው የሚገባውን ያህል ተሣትፎ እንዲያደርግ የሚያስችሉ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ተጨማሪ የግንዛቤ ሥራ አጠናክሮ መስራት እንደሚያስፈልግ፣ በማህበረ-ሰብ ተሣትፎ የሚገነቡ ት/ቤቶችን የጥራት ደረጃ ማስጠበቅ እንደሚገባና በተሣትፎው ላይ ወቅታዊና ተጨባጭ መረጃ መሰብሰብና ማደራጀት እንደሚያስፈልግ ታውቋል።

ያልተማከለ የትምህርት ሥርዓትና የአቅም ግንባታ ፕሮግራምን በተመለከተ በትምህርት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የማህበረሰቡን ውሣኔ ሰጭነትና ተሣታፊነት በማሳደግ ረገድ ያልተማከለ የትምህርት ሥርዓት ባለፈው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም አተገባበር ላይ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው፡፡ በመሆኑም የትምህርት የማቴሪል፣ የፋይናንስና የሰው፣ ኃይል አመራርና አስተዳደር ባልተማከለ ሥርዓት በወረዳ ደረጃ እንዲመራ ለወረዳዎች ብሎም ለቀበሌና ት/ቤቶች ከፍተኛ የአመራርና አስተዳደር ነጻነት ተሰጥቷል፡፡ መምህራንን፣ ርዕሣነ መምህራንንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን ከመቅጠርና ከመምራት አንስቶ በጀትን የማስተዳደር ሥልጣንና ኃላፊነት ለታችኛው የስልጣን እርከን በመሰጠቱ የትምህርት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን ቀልጣፋ አድርጎታል፣ የማህበረሰቡን ተሳትፎና የባለቤትነት

ስሜትም አሳድጎታል፣ ይህንንም ያልተማከለ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እስከ ት/ቤቶች ድረስ በርካታ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ሆኖም ግን የትምህርት ዘርፉን የልማት ፕሮግራሞች በተገቢው ሁኔታ ከማስፈጸም አንጻር በተለይ በወረዳ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ የአቅም ክፍተት በአንድ በኩል የሰለጠነ የሰው ኃይል መልቀቅና እጥረት ደግሞ በሌላ በኩል የሚታዩ ትላልቅ ችግሮች እንደሚታዩ ለመረዳት ተችሏል።

## ማጠቃለያ

በሦስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሐ ግብር የትግበራ ወቅት በአጠቃላይ ውጤታማና አበረታች ሥራዎች ቢከናወኑም አሁንም በቀጣይ መሰራት ያለባቸው ስራዎች አሉ። በመሆኑም የአራተኛውን የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሐ ግብር ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር የትምህርት ጥራትና አግባብነት፣ የትምህርት ፍትሃዊነትና ተደራሽነት እንዲሁም በትምህርት ዘርፉ በየደረጃው የመልካም አሰተዳደር ሙሉ በሙሉ ማስፈን ዋና ዋና የትኩረት መስኮቻችን ይሆናሉ፡፡ ይህንንም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ለቀጣዩ አምስት ዓመት ጠንክሮ መስራትን ይጠይቀናል።